# መንግሥት እና ቃል ኪዳን በአዲስ ኪዳን

## ትምህርት 2

## የእግዚአብሔር መንግሥት

Manuscript

thirdmill
Biblical Education. For the World. For Free.

© 2019 by Third Millennium Ministries

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። ከአሳታሚው የጽሑፍ ፈቃድ ውጭ ማጠቀሻነት፣ ለግምገማ ፣ ለአስተያየት ወይም ለትምህርት ዓላማዎች በአጭሩ መጠቀም ካልሆነ በስተቀር የዚህ ጽሑፍ ክፍል በማንኛውም መልኩ ወይም በማንኛውም መንገድ ለትርፍ ሊባዛ አይችልም። የአሳታሚው አድራሻ Third Millennium Ministries, Inc., 316 Live Oaks Blvd., Casselberry, Florida 32707.

በሌላ መንገድ ካልተጠቆመ በስተቀር፣ ሁሉም የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች  በ1954 ዓ.ም ከታተመው መጽሐፍ ቅዱስ  የተወሰዱ ናቸው።

## **ስለ**ሴርድሚል

እ.ኤ.አ. በ 1997 የተቋቋመው ፣ ሴርድሚል ለትርፍ ያልተቋቋመ የወንጌላዊ ክርስቲያናዊ አገልግሎት ሲሆን

**መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት፣ ለዓለም፣ በነጻ ይሰጣል።**

ግባችን በዓለም ዙሪያ በመቶ ሺዎች ለሚቆጠሩ ፓስተሮች እና ለአገልግሎት በቂ ሥልጠና ለሌላቸው የክርስቲያን መሪዎች ነፃ የክርስትና ትምህርት መስጠት ነው። በእንግሊዝኛ ፣ በአረብኛ ፣ በማንዳሪን ፣ በሩሲያኛ እና በስፓኒሽ ተወዳዳሪ የሌለውን የመልቲሚዲያ ሴሚናሪ ሥርዓተ ትምህርት በማዘጋጀት እና በዓለም አቀፍ ደረጃ በማሰራጨት ይህንን ግብ እያሟላን እንገኛለን። በአጋር መሥሪያ ቤቶቻችን አማካኝነት ሥርዓተ ትምህርታችን ከአሥር በላይ በሚሆኑ ሌሎች ቋንቋዎችም እየተተረጎመ ነው። ሥርዓተ ትምህርቱ በጥሩ ግራፊክ የተሠሩ ቪዲዮዎችን፣ የታተሙ ትምህርቶችን እና የበይነመረብ ግብዓቶችን ያካትታል። በትምህርት ቤቶች ፣ በቡድኖች እና በግለሰቦች ፣ በበይነመረብም ሆነ በትምህርት ማህበረሰቦች ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውል የተቀየሰ ነው።

ባለፉት ዓመታት፣ እጅግ በጣም ጥሩ ይዘትን እና ጥራትን የተሸለሙ የመልቲሚዲያ ትምህርቶችን ለማምረት ከፍተኛ ወጪ ቆጣቢ ዘዴን አዘጋጅተናል። ጸሐፊዎቻችን እና አርታኢዎቻችን በስነ-መለኮት የሰለጠኑ አስተማሪዎች ፣ ተርጓሚዎቻችን የሥነ-መለኮታዊ አስተውሎት ያላቸውና የሚተረጉሙበት ቋንቋዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሆናቸው  ናቸው ፣ እንሁም ትምህርቶቻችን ከዓለም ዙሪያ የመጡ በመቶዎች የሚቆጠሩ የተከበሩ የሴሚናሪ ፕሮፌሰሮች እና ፓስተሮች አሳቦችን ይዘዋል። በተጨማሪም ፣ የእኛ ግራፊክ ዲዛይነሮች ፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች እና አዘጋጆች ዘመናዊ መሣሪያዎችን እና ቴክኒኮችን በመጠቀም ከፍተኛውን የዝግጅት ደረጃዎችን የሚያሟሉ ናቸው።

የስርጭት ግቦቻችንን ለማሳካት ፣ ሴርድሚል ከቤተክርስቲያናት ፣ ከሴሚናሪዎች ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ፣ ከሚሲዮናውያን ፣ ከክርስቲያን ማሰራጫዎች እና ከሳተላይት ቴሌቪዥን አቅራቢዎች እና ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ስትራቴጂካዊ አጋርነት ፈጥሯል። እነዚህ ግንኙነቶች ቀደም ሲል ስፍር ቁጥር የሌላቸው የቪዲዮ ትምህርቶችን ለአገሬው ተወላጅ መሪዎች ፣ ለፓስተሮች እና ለሴሚናሪ ተማሪዎች ማሰራጨት አስችሏል። የድረ-ገጾቻችን እንዲሁ እንደ ስርጭት መንገዶች ሆነው ያገለግላሉ እንዲሁም  የመማሪያ ማህበረሰብ እንዴት እንደሚጀምሩ ግብዓቶቹንና ትምህርቶቻችንን ለማግኘት ተጨማሪ አገልግሎት ይሰጣሉ።

ሴርድሚል በ IRS እንደ 501 (ሐ) (3) ኮርፖሬሽን እውቅና ተሰጥቶታል። እኛ ገቢ የምናገኘው ከአብያተ-ክርስቲያናት ፣ ፋውንዴሽንስ፣ ንግድ ተቋማት እና ግለሰቦች በሚሰጡት አርዳታ ነው። ሰዎች ለእኛ ሲለግሱ ከሚከፍሉት ግብር ይቀነስላቸዋል። ስለአገልግሎታችን ተጨማሪ መረጃ ፣ እና እርስዎ እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉ ለማወቅ ፣ እባክዎ www.thirdmill.org ን ይጎብኙ።

# ማውጫ

**መግቢያ .......... 1**

**መልካም ዜና .......... 1**

ትርጉም .......... 2
የእግዚአብሔር መንግሥት .......... 3
የማይናወጥ ሉዓላዊነቱ .......... 4
የሚገለጥ የእግዚአብሔር መንግሥት .......... 4
የተስፋው ማደግ ጠቀሜታ .......... 5
የእስራኤል ውድቀቶች .......... 5
የእስራኤል ተስፋ .......... 6

**መምጣት .......... 9**

የሚጠበቁ ነገሮች .......... 9
የሦስት ገጽታዎች ድል .......... 14
ሽንፈት .......... 14
አርነት መውጣት .......... 18

**ማጠቃለያ .......... 21**

**አስተዋጽኦ ያደረጉ ጸሐፊዎች .......... 22**

**የቃላት ፍቺ .......... 23**

# መንግሥት እና ቃል ኪዳን በአዲስ ኪዳን

## ትምህርት ሁለት

## የእግዚአብሔር መንግሥት

## መግቢያ

በማንኛውም ጊዜ የተወሳሰበ ታሪክ በሚታነቡበት ጊዜ በብዙ ዝርዝሮች ውስጥ በቀላሉ ሊትጠፉ ትችላላችሁ። ነገር ግን ይህንን ችግር ለማስወገድ አንዱ መንገድ የታሪኩን በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ክፍሎች መለየት እና ከዚያም ደጋግሞ መጥቀስ ነው፤. ዋና ዋናዎቹን ነገሮች ግምት ውስጥ በማስገባት ዝርዝሮቹ እንዴት እንደሚጣመሩ ማየት መቻል ነው:: በብዙ መልኩ፣ የአዲስ ኪዳንን ሥነ-መለኮት ለመረዳት ሰንሞክር አንድ አይነት ነገር እውነት ነው። በእነዚህ ቅዱሳን ጽሑፎች ውስጥ መቆፈር ስንጀምር፣ ብዙ ዝርዝሮችን እናገኛቸዋለን፣ ስለዚህም መሰመራችንን ማጣት ቀላል ነው። ስለዚህ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና ሃሳቦች ለይተን ደጋግመን መጥቀስ አለብን።

ይህ መንግሥትና ቃል ኪዳን በአዲስ ኪዳን በሚለው ተከታታይ ትምህርታችን ውስጥ ይህ ሁለተኛው ትምህርታችን "የእግዚአብሔር መንግሥት" የሚል ርዕስ ሰጥተነዋል። በዚህ ትምህርት፣ ከአዲስ ኪዳን ዋና ዋና ትምህርቶች አንዱን ማለትም የእግዚአብሔርን መንግሥት እንጠቁማለን። እንደምንመለከተው፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ጭብጥ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በጣም አስፈላጊ ነው፤ ስለዚህ በትክክል መረዳት አለብን:: የአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት የመንግሥት ሥነ-መለኮት ነው። በሌላ አነጋገር፣ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች የጻፉት ነገር ሁሉ፣ በተወሰነ ደረጃ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስረዳት እና ለማስፋት ያደረ ነው።

በአዲስ ኪዳን ነገረ መለኮት የእግዚአብሔርን መንግሥት ታዋቂነት ከሁለት አቅጣጫዎች እንመረምራለን። በመጀመሪያ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች የመንግሥቱን የምሥራች ወይም ወንጌል ብለው የሰየሙትን እንመለከታለን። ሁለተኛ የመንግሥቱ መምጣት በጻፏቸው ነገሮች ሁሉ ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንዳሳደረ እንጠቁማለን። እነዚህ ሁለት ርዕሰ ጉዳዮች የእግዚአብሔር መንግሥት አስተምህሮ ሁሉንም የአዲስ ኪዳን ገጽታዎች እንደሚደግፍ ለማየት ይረዱናል። በመንግሥቱ ምሥራች እንጀምር::

## መልካም ዜና

አዲስ ኪዳንን የሚያውቅ ሰው ሁሉ የእርሱ ሥነ-መለኮት በጣም የተወሳሰበ እንደሆነ ያውቃል። ነገር ግን አንድ የአዲስ ኪዳን ትምህርት ካለ ሁሉም ሰው ለመረዳት እና በህይወት ላይ ተግባራዊ ለማድረግ መሞከር ያለበት፣ ወንጌል መሆን አለበት። እንዲያውም፣ ብዙዎቻችን የክርስቶስን ወንጌል ካልተረዳን፣ የአዲስ ኪዳንን ሥነ-መለኮት ገጽታ የመረዳት ችሎታችን በጣም የተገደበ እንደሆነ እንስማማለን። ይህ ግን ከባድ ጥያቄ ያስነሳል። በአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት ውስጥ ወንጌል፣ ወይም "የምሥራች" ወሳኝ የሆነው ለምንድነው? በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከሚገኙት ብዙ አስተምህሮዎች መካከል ለምን ጎልቶ ይታያል? እንደምንመለከተው፣ ወንጌል በአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት ውስጥ በጣም አስፈላጊ ነው ምክንያቱም በእግዚአብሔር መንግሥት ላይ ሰፋ ያለ ትምህርት ጋር የተገናኘ ስለሆነ ነው:: እናም ይህ ስለ እግዚአብሔር መንግስት የምስራች ትምህርት ሁሉንም የአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት ገጽታዎችን ይቀርፃል።

የመንግሥቱን ምሥራች በሦስት ደረጃዎች እንመለከታለን። በመጀመሪያ የምሥራቹን ትርጉም እንመለከታለን። ሁለተኛ የእግዚአብሔርን መንግሥት መሠረታዊ ጽንሰ ሐሳብ እንመረምራለን። ሦስተኛ የዚህን ጭብጥ እድገት አስፈላጊነት በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪክ ውስጥ እናያለን። በእግዚአብሔር መንግሥት የምሥራች ትርጉም እንጀምር።

## ትርጉም

> *የመንግሥቱ ወንጌል ስለ ንጉሡ ስለ ጌታ ስለ ተነገረልን የምሥራች የምንናገርበት መንገድ ነው። በተለይም፣ ስለ ኢየሱስ ስለ አዲስ ኪዳን የተነገሩትን መግለጫዎች ስናስብ፣ ይህ "ንጉሥ መጣ" የሚለው ማስታወቂያ ነው። ነገር ግን "ንጉሥ መጣ" ብቻ ሳይሆን ጌትነት፣ የኢየሱስ ንግሥና የታወጀው ሞቱና ትንሣኤው ንግሥናውን እንዳረጋገጡት ነው። ስለዚህ ምሥራቹ አስቀድሞ የሆነ ነገር ማወጅ የሆነበት ስሜት አለ። እንዴት እንደምንኖር አንድምታ አለው። ነገር ግን መልካም ዜና ኢየሱስ መጣ; ሞትን በመሞት አሸንፎአል። ስለዚህ እግዚአብሔር አስቀድሞ እንደ ሆነ ይህን የምሥራች ነግሮናል። ሆኖም ምሥራቹ ለዘላለም የሚፈጸሙት ተስፋዎች አሉት።*
>
> — ዶር. ሪቻርድ ሊንትስ

በሉቃስ 4፡43፣ ኢየሱስ የአገልግሎቱን ዓላማ በዚህ መንገድ ጠቅለል አድርጎ ገልጿል።

> እርሱ ግን። ስለዚህ ተልኬአለሁና ለሌሎቹ ከተማዎች ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል እሰብክ ዘንድ ይገባኛል አላቸው። (ሉቃስ 4:43).

በሉቃስ 4:43 ላይ "ምሥራች" የሚለው ቃል አንድ ጊዜ ብቻ የተገለጸ ቢሆንም፣ የምሥራቹ ጽንሰ-ሐሳብ በዚህ ቁጥር ውስጥ ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል። "ምሥራች" የሚለው ሐረግ የመጣው ኢቫንግሊዮን ከሚለው የግሪክኛ ስም ሲሆን ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ 76 ጊዜ ያህል ተጠቅሷል። የ ኢቫንግሊዮን ሥርወ-ቃሉ እንደ "መልካም ማስታወቂያ" ወይም "ጥሩ መልእክት" ማለት እንደሆነ ይጠቁማል።

ሆኖም ኢየሱስ በዚህ ጥቅስ ላይ "ምሥራቹን መስበክ እንዳለበት" ተናግሯል። "አዋጅ" ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ግስ ኢቫንግሊዞ ነው። ይህ ቃል ኢቫንግሊዮን ከሚለው ተመሳሳይ የግሪክ ቃላት ቤተሰብ የመጣ ሲሆን ትርጉሙም "ምሥራቹን መስበክ ወይም ማወጅ" ማለት ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ 54 ጊዜ ያህል ተጠቅሷል። የእነዚህ ቃላት ድግግሞሽ ይህ ጽንሰ-ሐሳብ ለአዲስ ኪዳን ደራሲዎች ምን ያህል አስፈላጊ እንደነበረ ያሳያል።

ዛሬ ብዙ ወንጌላውያን ምሥራቹን ወይም ወንጌልን አንድ ሰው በክርስቶስ መዳንን ለማግኘት ሊወስዳቸው ስለሚገቡ እርምጃዎች ማብራሪያ አድርገው ያስባሉ። ይህ ግን ኢየሱስ በአእምሮው ይዞት የነበረው ሃሳብ አልነበረም። የክርስቶስ ተከታዮች መሆን የምንችልበትን መንገድ ለመካፈል ዝግጁ መሆን የሚገባን ያህል በቅዱሳን ጽሑፎች ውስጥ የሚገኘው ምሥራች ግን ይበልጥ ጉልህ የሆነ ነገር ስላለው ነገር ይናገራል። እንደምናየው፣ የማንኛውንም ግለሰብ ወይም ቡድን መዳን ከመጥቀስ ይልቅ፣ ወንጌል የእግዚአብሔር መንግሥት የድል ወንጌል ነው።

ይህንንም ለመረዳት የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች "ምሥራቹን አውጁ" የሚለውን አገላለጽ ከሴፕቱጀንት የብሉይ ኪዳን የግሪክኛ ትርጉም የወሰዱ መሆናቸውን መገንዘብ አለብን። ሴፕቱጀንት ቀደም ብለን የጠቀስነውን ኢቫንግሊዞ የተባለውን ግስ 20 ጊዜ ያህል ይጠቀማል። ይህ ቃል ባሳር የተባለውን የዕብራይስጥ ግስ የተተረጎመ ሲሆን ትርጉሙም "ምሥራች ማምጣት ወይም ማወጅ" ማለት ነው። ነገር ግን፣ እንደ 1ኛ ሳሙኤል 31፡9 እና 2ሳሙ 18፡19 ያሉት ምንባቦች እንደሚያመለክቱት እነዚህ ቃላት ስለ ነገሥታትና መንግሥታት ሲነገሩ፣ በጦርነት ውስጥ የድልን የምሥራች ያመለክታሉ። ይህ ምልከታ አስፈላጊ ነው ምክንያቱም በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለው "ምሥራች" ብዙውን ጊዜ ከእግዚአብሔር መንግሥት ድል ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በተግባር፣ በሉቃስ 4፡43፣ ኢየሱስ ሲናገር፡-

> እርሱ ግን። ስለዚህ ተልኬአለሁና ለሌሎቹ ከተማዎች ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል እሰብክ ዘንድ ይገባኛል አላቸው። (ሉቃስ 4:43).

ይህንን መግለጫ በእውነቱ በእነዚህ መስመሮች መተርጎም እንችላለን-

> እርሱ ግን። ስለዚህ ተልኬአለሁና ለሌሎቹ ከተማዎች ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት (ድል) ወንጌል እሰብክ ዘንድ ይገባኛል አላቸው። (ሉቃስ 4:43).

አዲስ ኪዳን ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የድል የምሥራች ሲናገር፣ በዚህ ትምህርት በኋላ እንደምናየው፣ ልዩ የሆነ ድልን ያመለክታል። ስለዚህ መጀመሪያ ላይ እንግዳ ቢመስልም፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለው የምሥራቹ ወይም የወንጌል መሠረታዊ ጽንሰ-ሐሳብ የእግዚአብሔር መንግሥት "[ድልን]" የምሥራች መሆኑን መቀበል አለብን።

የመንግሥቱ ምሥራች ለእግዚአብሔር መንግሥት የድል የምሥራች ማለት እንደሆነ ከተመለከትን፣ አሁን የእግዚአብሔርን መንግሥት መሠረታዊ ጽንሰ ሐሳብ ለመዳሰስ ተዘጋጅተናል።

## የእግዚአብሔር መንግሥት

የእግዚአብሔር መንግሥት በተለይ በአዲስ ኪዳን ቢያንስ ሰባት ጊዜ ከወንጌል ጋር የተያያዘ ነው። "የመንግሥቱን ምሥራች" የሚለውን አገላለጽ በትንሹ ልዩነት ብቻ በማቴዎስ 4:23; 9:35; እና 24:14; በሉቃስ 4:43; 8:1; እና 16:16; እና በሐዋርያት ሥራ 8:12 እናያለን። ይህ ድግግሞሽ ወንጌልን - ወይም የድልን መልእክት - ከእግዚአብሔር መንግሥት ጋር የማገናኘት አስፈላጊነትን ያመለክታል። ይህንን ለመረዳት ግን በመጀመሪያ ኢየሱስና ተከታዮቹ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ሲናገሩ ምን ማለታቸው እንደሆነ መረዳት አለብን።

> የእግዚአብሔር መንግሥት በእግዚአብሔር ቦታ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የእግዚአብሔር አገዛዝ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ ላይ በዘፍጥረት 1 እና 2 ውስጥ የእግዚአብሔር ሰዎች አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ሲኖራቸው እግዚአብሔር ገዥ እንደሆነ እና በኤደን ገነት ውስጥ በእግዚአብሔር ቦታ እንዳሉ እናያለን። ከዚያም፣ በኃጢአት ምክንያት ያ የተመሰቃቀለ ሆነ ነገር ግን እግዚአብሔር መንግስቱን ይመሰርታል፣ በመጀመሪያ በአብርሃም እና በአብርሃም ዘሮች፣ እና በመጨረሻም ከግብጽ ከወጡ በሙሴ በኩል ከእስራኤል ህዝብ ጋር መንግሥቱን መሠረተ፡፡ ይህ የእግዚአብሔር አገዛዝ በእግዚአብሔር ሕዝብ በእስራኤል እና በመጨረሻ በእግዚአብሔር ቦታ በከነዓን ምድር ላይ ነው። ነገር ግን ያ አቅጣጫ ከክርስቶስ መምጣት ጋር በበለጠ ፍጻሜውን ሲያገኝ እናያለን፣ እናም እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል እንደ ንጉሱ፣ የተሾመው ንጉስ ሲገዛ እናያለን። የእግዚአብሔርም ሕዝብ አይሁድንና አሕዛብን ከአሕዛብ ሁሉ ከነገዶችም ከቋንቋም የተውጣጡ ሰዎች ናቸው ነገር ግን የእግዚአብሔር ቦታ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ናት፤ ሰማያዊት ቤታችን እንጂ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ አይደለም… ስለዚህ በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር መንግሥት አሁን አለ በክርስቶስ በሕዝቡ ላይ ከሁሉም ነገዶች፣ ብሔረሰቦች እና ቋንቋዎች የተውጣጡ፣ በዓለም ሁሉ ተበታትነው በአንድ የተወሰነ ቦታ፣ ጂኦግራፊያዊ ቦታ ላይ ሳይሆን በሰማያዊ ስፍራ፣ መንፈሳዊ መኖሪያችን እናያለን። ነገር ግን በዚያን ጊዜ፣ አዲስ ኪዳን፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ኢየሱስ በሚመለስበት ጊዜ ምን እንደሚመስል ፍንጭ ይሰጠናል፣ እናም ያ መንግሥት አሁን በዚህ ዓለም ውስጥ በተወሰነ መጠን ተደብቆ ያለ ሲሆን፣ ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ በግልጽ ይታያል። ጉልበት ሁሉ ይንበረከካል ምላስም ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክራል እግዚአብሔርም በንጉሱ በክርስቶስ በኩል በሚያውቁት በህዝቡም ላይ ፍጹም በሆነ መልኩ በሰማያዊቷ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ይነግሣል ።
>
> — ዶክተር ቆስጠንጢኖስ አር ካምቤል

ቅዱሳት መጻሕፍት የእግዚአብሔርን መንግሥት በሁለት ዋና መንገዶች ይጠቅሳሉ። በአንድ በኩል፣ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የማይናወጥ የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ወይም በፍጥረት ሁሉ ላይ ስላለው የማይለወጥ አገዛዙ ብዙ ጊዜ ይናገራል። እርሱም የሚገለጠው መንግሥቱንና አምላክ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ንግሥናውን የገለጠበትን መንገድ ያመለክታል። መጀመሪያ የማይናወጥ ሉዓላዊነቱን እንመልከት።

## የማይናወጥ ሉዓላዊነቱ

እንደ 1ኛ ዜና 29፡11 እና 1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡15 ያሉት ምንባቦች ስለ ፍጥረታት ሁሉ እንደ እግዚአብሔር መንግስት ይናገራሉ ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁል ጊዜ የሚገዛ እና የሚገዛው በፈጠረው ሁሉ ላይ ነው። ቅዱሳን ጽሑፎች ስለ እግዚአብሔር ሉዓላዊነት የሚናገሩት በሰማይም ሆነ በምድር በሁለት ደረጃዎች እንደሆነ መዘንጋት የለብንም።

ስለ መንግሥተ ሰማያት፣ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ 1 ነገሥት 8፡27 ባሉ ቦታዎች ላይ ስለ እግዚአብሔር ንግሥና ይናገራሉ። ሰሎሞን በዚህ ጥቅስ ላይ "ሰማያትና ከፍተኛው ሰማይ" "[አምላክን] ሊይዝ የማይችል" የተፈጠረ ቦታ እንደሆነ በግልጽ ተናግሯል። እግዚአብሔር ግን አሁንም ዝቅ ብሎ በዚያ በፍጥረቱ ፊት ራሱን ገለጠ።

እንደ ኢሳያስ 6፡1; 2 ዜና መዋዕል 18:18; ኢዮብ 1:6; መዝሙረ ዳዊት 82:1; እና ዳንኤል 7:9-10; እንዲሁም እንደ ሉቃስ 22፡30 ያሉ የአዲስ ኪዳን ምንባቦች; እና ራዕይ 4-6 ሰማይ ከሚታየው አለም በላይ ሁሉም አይነት ተግባራት የሚከናወኑበት የእግዚአብሔር ቤተ መንግስት እንደሆነ ያመለክታሉ። እግዚአብሔር በሰማይ በዙፋን ላይ እንደተቀመጠ፣ ሪፖርቶችን ይቀበላል፣ ጸሎቶችን ይሰማል፣ ያሰበውን ያዘጋጃል፣ እቅድ ያወጣል እና ንጉሣዊ ድንጋጌዎችን ያወጣል። መንፈሳዊ ፍጥረታትን በምድር ላይ ተልዕኮውን እንዲፈጽሙ ያዛል። አልፎ ተርፎም በልዩ ሁኔታ የተመረጡትን የሰው ልጆች በራዕይ ወደ ቤተ መንግሥቱ እንዲገቡ ያደርጋል፣ ለአገልግሎቱም አደራ ይሰጣል። በሰማያዊው ፍርድ ቤት ጥፋተኛነትን እና ንፁህነትን ያውጃል እንዲሁም በመንፈሳዊ ፍጥረታት፣ በግለሰብ ሰዎች እና በአሕዛብ ላይ እንደ ፍርዱ እና እንደ ምህረቱ ይፈርዳል። ነገር ግን የእግዚአብሔር ሰማያዊ ተግባራት መንግሥቱን በሰማያት ብቻ የሚመሩ አይደሉም። እርሱ ደግሞ በፍጥረቱ ዝቅተኛ ግዛቶች ውስጥ - በምድር ላይ ሉዓላዊ ነው፡፡

ምንም እንኳን ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ እግዚአብሔር መንግሥት በሰማይም በምድርም የማይናወጥ የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ቢናገሩም፣ ኢየሱስ እና የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች በምድር ላይ ስላለው የእግዚአብሔር መንግሥት ሲናገሩ፣ የሚገለጥ የእግዚአብሔር መንግሥት ብለን የጠራነውን በልቡናቸው ይዘዋል። እና እግዚአብሔር በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ መንግሥቱን እንዴት እንደገለጠ ማየት የምንችለው በዚህ ምድራዊ ግዛት ውስጥ ነው።

## የሚገለጥ የእግዚአብሔር መንግሥት

አሁን፣ ልክ እንደተናገርነው፣ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ፍጥረቱን ሙሉ በሙሉ ይቆጣጠራል እና ሁልጊዜም ይኖራል። ነገር ግን እየተገለጠ ያለው የእግዚአብሔር መንግሥት የሚያመለክተው እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ በፍጥረት ላይ ያለውን ሉዓላዊነት የሚገልጥበትን፣ የሚያሳየውን የተለየ መንገድ ነው። ስለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት እግዚአብሔር በሰማይ ንግሥናውን እንዴት እንደገለጠ ቢያረጋግጡም፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ግን አብዛኛውን ትኩረታቸውን የሰጡት እግዚአብሔር በምድር ላይ ንግሥናውን እንዴት እንደገለጠ ለማስረዳት ነው።

በመጀመሪያ፣ እግዚአብሔር ንግሥናውን በኤደን ገነት ውስጥ በግልጽ አሳይቷል። የመጀመሪያዎቹን የሰው ልጆች በዚያ በተቀደሰ የአትክልት ስፍራ አስቀምጦ የሚታየውን መንግሥቱን በዓለም ሁሉ እንዲያሰፉ አዟቸዋል። ምድርን እንደ ንጉሣዊ እና ካህናት የእግዚአብሔር አምሳሎች እንዲሞሉ እና እንዲገዙ ነበር፡፡ ነገር ግን ሰይጣን አዳምና ሔዋንን በመንግሥቱ ላይ ትልቅ ውድቀት ውስጥ እንዲገቡ አድርጓቸዋል። በምላሹ, እግዚአብሔር ፍጥረቱን ረገመው እና የሰውን ልጅ ተግባር የበለጠ ከባድ አድርጎታል፡፡ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉትን እና ሰይጣን በአእግዚአብሔር ላይ ባደረገው ማመፁን የቀጠሉትን የሰው ልጆችን በሁለት ተቀናቃኝ ቡድኖች ከፈለ።

ይህ ፉክክር በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪክ ውስጥ ብዙ መልክ የያዘ እና ለእግዚአብሔር መንግሥት ብዙ ፈተናዎችን ያስተከተለ ነው። ይሁን እንጂ ቅዱሳን ጽሑፎች እግዚአብሔር በመጨረሻ እርሱን የሚቃወሙትን ሁሉ እንደሚያሸንፍ ደጋግመው ያሳያሉ። የእርሱ አምሳል ምድርን በመሙላት እና በመግዛት ይሳካል፣ እናም የእግዚአብሔር መንግስት ድንቅ ነገሮች በሁሉም ቦታ ይገለጣሉ። እናም በዚያን ጊዜ፣ እግዚአብሔር በአመፅ ሁሉ ላይ ያለው ድል እጅግ ታላቅ ይሆናል፣ እናም እያንዳንዱ ፍጥረት እርሱን የፍጥረት ንጉስ እንደሆነ እውቅና ይሰጣል። ሐዋርያው ጳውሎስ በፊልጵስዩስ 2፡10-11 እንደገለጸው፡

ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፥ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው። (ፊልጵስዩስ 2፡10-11).

ይህ አስደናቂ የታሪክ ግብ ራዕይ ኢየሱስና ተከታዮቹ "የእግዚአብሔር መንግሥት ምሥራች" በማለት ያወጁት ድል ነው።

መልካሙንም ሆነ የእግዚአብሔርን መንግሥት በመመልከት የመንግሥቱን የምሥራች መሠረታዊ ፅንሰ-ሀሳብ ከቀረፅን፣ ወደዚህ የእግዚአብሔር መንግሥት የድል ማወጅ አስፈላጊነት ልንሸጋገር ይገባል።

## የተስፋው ማደግ ጠቀሜታ

የመንግሥቱ የድል ምሥራች ከአዲስ ኪዳን ነገረ መለኮት ጋር እንደ ድርና ማግ የገመደ በመሆኑ በአዲስ ኪዳን በሁሉም ቦታ በግልጽም ሆነ በተዘዋዋሪ ይታያል። አዲስ ኪዳን በተጻፈበት ጊዜ፣ ለእግዚአብሔር መንግሥት ያለው የድል ተስፋ ትልቅ ጠቀሜታ ስላለው በሁሉም የአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት ገጽታዎች ውስጥ ዘልቆ ነበር።

በአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት ውስጥ የእግዚአብሔርን መንግሥት ማደግን ማየት የምንችልባቸው ብዙ መንገዶች አሉ፣ ነገር ግን ለዓላማዎቻችን ሁለት ገጽታዎችን ብቻ እንመለከታለን። በመጀመሪያ የእስራኤልን ውድቀት እስከ አዲስ ኪዳን ዘመን ድረስ እንመለከታለን። ሁለተኛ ከክርስቶስ መምጣት በፊት እስራኤል ለመንግሥቱ ያላቸውን ተስፋ እንመረምራለን። በመጀመሪያ ስለ እስራኤል ውድቀት እናስብ።

### የእስራኤል ውድቀቶች

ኃጢአት ፍጥረትንና የሰውን ዘር እርግማን ካመጣ በኋላ፣ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ለአዳምና ለሔዋን የሰጣቸውን የመንግሥት ተልእኮ እንዲፈጽሙ አብርሃምንና ዘሩን መረጠ። እግዚአብሔር የአብርሃምን ቤተሰብ እንደሚያበዛ ቃል ገባ። የእግዚአብሔርን በረከቶች በመላው ዓለም ለማዳረስ እንደ መነሻ ለአብርሃም ዘሮች የተስፋይቱን ምድር ሰጣቸው። በሙሴና በኢያሱ ዘመን፣ እስራኤላውያን ከነዓናውያንና ከነዓናውያን በሚያገለግሉት የሰይጣን መናፍስት ላይ ድል በማድረግ እስራኤላውያን ያላቸውን መብቶችና ኃላፊነቶች አበረታቷል። በኋላ፣ ዳዊት፣ ሰሎሞን እና ሌሎች ጥቂት የእስራኤል እና የይሁዳ ነገሥታት የእግዚአብሔርን መንግሥት ለሌሎች ሕዝቦች




እግዚአብሔር የመንግሥቱን ተልእኮ እንዲፈጽሙ አብርሃምንና ዘሩን መረጠ።

በማስፋፋት ረገድ ጉልህ ስኬት አግኝተዋል። በእርግጥ፣ በሰለሞን የግዛት ዘመን ከፍተኛ ደረጃ ላይ በነበረበት ወቅት፣ እስራኤል ከዓለም እጅግ የከበሩ ግዛቶች አንዷ ነበረች።

እነዚህ ሙብቶች ቢኖሩም እያንዳንዱ የአብርሃም ዘሮች እግዚአብሔርን በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ወድቀዋል። ነገር ግን እግዚአብሔር ትዕግሥትን አሳይቷል እናም ኃጢአታቸው ቢኖራቸውም ወደፊት እንዲራመዱ አስችሏቸዋል፡፡ በሚያሳዝን ሁኔታ፣ አንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ሕዝቦች የራሳቸው መንግሥት ሲሆኑ፣ ንጉሣዊ ሥርወ መንግሥትና በዋና ከተማው ውስጥ ቤተ መቅደስ ሲኖራቸው፣ የእስራኤል ውድቀት በጣም ጎልቶ እስኪታይ ድረስ እግዚአብሔር ፈርዶባቸዋል። የአሦር እና የባቢሎን ክፉ ግዛቶች እስራኤልን በጦርነት እንዲያሸንፉ ጥሪ አቀረበ። እነዚህ ከባድ ሽንፈቶች በመጨረሻ የዳዊትን ቤት አስወገዱ፣ ቤተ መቅደሱን አወደሙ፣ ኢየሩሳሌምን አወደሙ እና አብዛኞቹን እስራኤላውያን በግዞት ወሰዱ። የተስፋይቱ ምድር ፈርሳ ቀርታለች። እና በብሉይ ኪዳን መጨረሻ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ስኬቶች ሁሉም የጠፉ ይመስሉ ነበር። በአዲስ ኪዳን ዘመን፣ በእስራኤል የነበረው የእግዚአብሔር መንግሥት በአህዛብ ሕዝቦች እና በሚያገለግሉት የሐሰት ሰይጣናዊ አማልክቶች ሥር ከ500 ለሚበልጡ ዓመታት መከራ ደርሶባታል።

እንደ አለመታደል ሆኖ፣ የዘመናችን ክርስቲያኖች ከእነዚህ ተሞክሮዎች በጣም የራቁ በመሆናቸው አብዛኞቻችን በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር መንግሥት ሽንፈት በአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ እንዳሳደረ አናውቅም። ሆኖም እስራኤላውያን ለአሕዛብ ሕዝቦች መገዛታቸው የኢየሱስ ተከታዮችን ጨምሮ በመጀመሪያው መቶ ዘመን በነበሩት አይሁዶች አእምሮ ላይ ከባድ ጫና አሳድሮባቸው ነበር። የመጀመሪያው መቶ ዘመን አይሁዳውያን፣ ምርኮው የሚታየው የእግዚአብሔር መንግሥት መጨረሻ ነበርን? ለእግዚአብሔር መንግሥት ተስፋ ያለው የምሥራች ነበረን? ይህ ሁኔታ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች የእግዚአብሔር መንግሥት አላበቃም ብለው እንዲከራከሩ አድርጓቸዋል። ሁሉም አልጠፋም። የናዝሬቱ ኢየሱስ ግዞቱ እንደሚያበቃ ምሥራቹን ሰበከ። እና የእስራኤል ውድቀቶች ቢኖሩም፣ አሸናፊው የእግዚአብሔር መንግሥት በዓለም ሁሉ በክርስቶስ ይመሰረታል።

በእስራኤል ውድቀቶች የመንግሥቱን አስፈላጊነት ከተመለከትን፣ ከምርኮ በኋላ እስራኤል ለእግዚአብሔር መንግሥት ያላቸውን ተስፋ ለመመልከት ዝግጁ ነን።

**የእስራኤል ተስፋ**

በብሉይ ኪዳን፣ እስራኤል ታማኝ ባለመሆናቸው ሽንፈትና ስደት ሊደርስባቸው እንደሚችል ለማስጠንቀቅ እግዚአብሔር በነቢያቱ ተናግሯል። ነገር ግን፣ በምህረቱ፣ እንዲሁም በስደት ያሉትን ታላቅ ድል ተስፋ በማድረግ ንስሃ እንዲገቡ ነቢያትን አነሳስቷቸዋል። እነዚህ ትንቢቶች ውስብስብ ነበሩ፣ ነገር ግን በጥቅሉ ሲታይ፣ እስራኤል እግዚአብሔር ጠላቶቹን ድል የሚያደርግበትን እና ሕዝቡን ወደ ክብር፣ ዓለም አቀፋዊው መንግሥቱ በረከቶች የሚያስገባበትን ጊዜ ተስፋ ያደርጉ ነበር።

እነዚህን ተስፋዎች በብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ውስጥ ብዙ ቦታዎችን ማየት እንችላለን፣ ነገር ግን ለጊዜው፣ በኢሳይያስ 52 ላይ ከሚታወቀው ትንቢት ውስጥ ሁለት ጥቅሶችን ብቻ እንመለከታለን። በመጀመሪያ፣ በኢሳይያስ 52፡7 እናነባለን፡

> *የምስራች የሚናገር፥ ሰላምንም የሚያወራ፥ የመልካምንም ወሬ የምስራች የሚናገር፥ መድኃኒትንም የሚያወራ፥ ጽዮንንም። አምላክሽ ነግሦአል የሚል ሰው እግሩ በተራሮች ላይ እጅግ ያማረ ነው። (ኢሳይያስ 52:7).*

ይህ ጥቅስ ለእኛ አስፈላጊ ነው ምክንያቱም የእግዚአብሔርን መንግሥት የድል ምሥራች በግልጽ ይጠቅሳል። በተጨማሪም ኢሳይያስ ተመሳሳይ መግለጫ ከተናገረበት ከኢሳይያስ 40:9 ጋር ተመሳሳይ ነው። በእነዚህ ሁለት ምንባቦች ውስጥ ያሉት ትልልቅ አውዶች "ምሥራቹ" የሚያመለክተው ከእስራኤል ግዞት በኋላ ታይቶ የማይታወቅ የእግዚአብሔር መንግሥት ድል ነው። እነዚህ ተስፋ ሰጭ ትንቢቶች በአንደኛው መቶ ዘመን የነበሩት አብዛኞቹ አይሁዳውያን ሥነ-መለኮታዊ ነጸብራቅ ውስጥ ገብተዋል። የአዲስ ኪዳንን ሥነ-መለኮት ዘልቀው መግባታቸው የሚያስገርም አይደለም።

> *የብሉይ ኪዳን ትረካ በአጠቃላይ በምርኮ መሪነት የተገዛ ነው። ከአዳም እና ከሔዋን ጋር ወደ ኤደን ገነት ይመለሳል፣ እና ያ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ እንደገና ተቀርጿል። እናም፣ በብሉይ ኪዳን ትረካ ውስጥ ትልቅ ደረጃ ላይ የሚታየው የዚህ አይነት ተስፋ አስቆራጭ የሁኔታዎች ለውጥ፣ በተፈጥሮ ከግዞት በላይ የሆነ ተስፋ ፍላጎትን ያሳያል። ስለዚህ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚመልስ በተለይ በኢሳይያስ ውስጥ ብዙ በቅርብ ጊዜ የሚነገሩ ትንቢቶች አሉን፣ ነገር ግን ያንን ወደ ፍጥረት ትረካ ስትመለስ፣ ወደ መሬት መመለስ ብቻውን የመጀመሪያውን ሁኔታ ለመቀልበስ በቂ እንዳልሆነ ትገነዘባለች። በመጀመሪያ ወይም ከመጀመሪያው በኋላ ብዙም ሳይቆይ የደረሰ ጉዳት… እናም፣ በብሉይ ኪዳን ነቢያት ለእስራኤል በቅርብ ጊዜ ልዩ ተስጥዖ ባለው ንጉሳዊ እጅ ነጻ መውጣት መሻት ነበራቸው፤ እንዲሁም ምናልባትም በመጨረሻ የእግዚአብሔር ሕዝብ ንጉሣዊ ተወካይ ከሆነውም።*
>
> — ዶክተር ሾን ማክዶን

ኢሳይያስ 52:7ን በጥልቀት ስንመረምር እስራኤል ለእግዚአብሔር መንግሥት ድል ካላቸው ተስፋ ጋር የተያያዙ አራት ገጽታዎችን ጎላ አድርጎ ይገልጻል።

በመጀመሪያ ኢሳይያስ መልእክተኞች 'ምሥራች እንደሚያመጡ' እና ለጽዮን 'ምሥራች እንደሚያመጡ' ተናግሯል። እነዚህ ሁለቱም ሀረጎች ሴፕቱጀንት በኢቫንግሊዞ የተተረጎመውን ባሳር የሚለውን የዕብራይስጥ ግስ ነው። ቀደም ሲል እንዳየነው፣ ይኸው የቃላት አነጋገር በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለእግዚአብሔር መንግሥት በክርስቶስ የድል ምሥራች ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

ሁለተኛ በሮሜ 10፡15 ላይ ኢሳ 52፡7 ተጠቅሶ እናያለን። እዚህ ላይ ጳውሎስ የክርስቲያን ስብከት ኢሳይያስ የእስራኤል ግዞት ሲያበቃ መልእክተኞች ምሥራቹን እንደሚያውጁ የተናገረው ትንቢት ፍጻሜውን እንዳገኘ አመልክቷል።

ሦስተኛ ኢሳይያስ የምሥራቹ "የሰላም" እና "የመዳን" አዋጅ እንደሚሆን ተንብዮአል። በኤፌሶን 6፡15 ላይ፣ ጳውሎስ የክርስቲያኑን "የሰላም ወንጌል" በመጥቀስ በኤፌሶን 1፡13 ላይ "የመዳናችሁን ወንጌል" ጠቅሷል።

አራተኛው የዚህ ጥቅስ የመጨረሻ መስመር "አምላክህ ነገሠ!" ሲል ምሥራቹን ጠቅለል አድርጎ ይገልጻል። ይህ መልእክት ኢየሱስና የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች "የመንግሥቱን ምሥራች" ማለትም "የእግዚአብሔርን" በማለት ደጋግመው የገለጹት የወንጌል መሠረት ነው።

በኢሳይያስ 52:7 ላይ ኢሳይያስ ስለ እስራኤል ተስፋ እንዴት እንደሚመጣ ትንቢት እንደተናገረ አይተናል፣ እስቲ በዚያው ምዕራፍ ቁጥር 10 ላይ እንይ። እዚህ ላይ፣ እስራኤል ለማየት የምትጓጓውን ሁለቱን የድል ገጽታዎች ኢሳያስ ተንብዮአል። በመጀመሪያ የእግዚአብሔር ጠላቶች እንደሚሸነፉ አስቀድሞ ገምቷል።

የእግዚአብሔር ጠላቶች ሽንፈት በኢሳይያስ 52፡10 የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ ኢሳይያስ እንዲህ ሲል ተናግሯል፡

> እግዚአብሔር የተቀደሰውን ክንዱን በአሕዛብ ሁሉ ፊት ገልጦአል፥ በምድር ዳርቻ የሚኖሩትም ሁሉ የአምላካችንን መድኃኒት ያያሉ። (ኢሳይያስ 52:10).

እዚህ ላይ እግዚአብሔር "የተቀደሰውን ክንዱን እንደሚዘረጋ" ማለትም ጠላቶቹን ድል ለማድረግ በጦርነት ውስጥ ያለውን የጥንካሬ ክንዱን እንደሚገልጥ እንመለከታለን።

እርግጥ ነው፣ ብሉይ ኪዳንን የሚያውቁ ሁሉ እግዚአብሔር ጠላቶችን ብዙ ጊዜ እንዳሸነፈ ያውቃሉ። ስለዚህ ስለ አምላክ ድል የሚናገረው ትንቢት ልዩ ያደረገው ምንድን ነው? በዚህ ጥቅስ ላይ ኢሳይያስ እግዚአብሔር ጠላቶቹን "በሕዝቦች ሁሉ ፊት" እንደሚያሸንፍ ተንብዮአል። በሌላ አነጋገር፣ ኢሳይያስ ከእስራኤል ምርኮ በኋላ እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ ያሉትን ጠላቶቹን ሙሉ በሙሉ እንደሚያሸንፍ ተንብዮ ነበር። ኃይላቸውን ያጠፋል፣ ከምድርም ያስወግዳቸዋል፣ እናም ወደ ዘላለማዊ ፍርድ ይልካቸዋል።

ሁለተኛ የኢሳይያስ 52፡10 የመጨረሻ አጋማሽ የእግዚአብሔር ድል የእግዚአብሔርን ሕዝብ ወደ መንግሥቱ በረከቶች ነጻ እንደሚያወጣም ይነግረናል። ይህን የኢሳይያስ 52፡10 ክፍል አድምጡ፡

> …በምድር ዳርቻ የሚኖሩትም ሁሉ የአምላካችንን መድኃኒት ያያሉ። (ኢሳይያስ 52:10).

እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ሕዝቡን ደጋግሞ እንዳዳነ እናውቃለን። ሆኖም ኢሳይያስ እዚህ ላይ በተነበየው መዳን ውስጥ "የምድር ዳርቻዎች ሁሉ" ያዩታል። የእግዚአብሔር ጠላቶች ሽንፈት ዓለም አቀፋዊ እንደሚሆን ሁሉ ነፃነቱም ዓለም አቀፋዊና የመጨረሻ ይሆናል። በመጨረሻ፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ መንግሥቱ ወደ ደስታ፣ ፍቅር፣ ጽድቅ፣ ሰላም፣ ብልጽግና እና በክብር ጎላዌው ወደ ማለቂያ የሌለው ደስታ ያሳልፋቸዋል።

በትምህርታችን እነዚህን ሁለት የእግዚአብሔር የድል ገጽታዎች በጥልቀት እንመለከታቸዋለን፣ ነገር ግን እነዚህ ጥቅሶች እንደሚገልጹት፣ የመጪው መንግሥት ትንቢቶች በብሉይ ኪዳን ውስጥ ይታያሉ።

እንደ አለመታደል ሆኖ፣ ከ2,000 ለሚበልጡ ዓመታት፣ ትውፊታዊ የክርስትና ሥነ-መለኮት በአዲስ ኪዳን የመንግሥቱን ታዋቂነት አጨልሞታል። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት ክርስቲያኖች ለተለያዩ ጉዳዮች ምላሽ ለመስጠት የተለያዩ ሥነ-መለኮታዊ አመለካከቶችን በትክክል አፅንዖት ሰጥተዋል። ነገር ግን ሁልጊዜ አዲስ ኪዳን ሲጻፍ የእግዚአብሔር መንግሥት ሽንፈት በኢየሱስ ተከታዮች ላይ ከባድ እንደነበር ማስታወስ አለብን። የእግዚአብሔር መንግሥት በኢየሱስ ታይቶ በማይታወቅ ድል እንደሚቀዳጅ ከማመን የበለጠ አስፈላጊ ነገር አልነበረም። በዚህም ምክንያት፣ የአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት በእግዚአብሔር መንግሥት የምሥራች ማዕቀፍ ውስጥ ተጥሏል።



ቪዲዮዎችን፣ የትምህርት መመሪያዎችና ሌሎች ግብዓቶችን ለማግኘት Thirdmill at thirdmill.org. ይመልከቱ

እስካሁን ባለው በዚህ የእግዚአብሔር መንግሥት ትምህርት፣ የመንግሥቱን የምሥራች ዋና ጭብጥ በአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት ውስጥ አስተዋውቀናል። እንግዲህ፣ ወደ ሁለተኛው ዋና ርዕሳችን እንሸጋገር፡ የመንግሥቱ መምጣት የአዲስ ኪዳንን ሥነ መለኮት እንዴት እንደቀረጸ እንመልከት።

## መምጣት

ሁላችንም አንዳንድ ነገሮች ሊፈጸሙ ነው ብለን የምናምንበት ጊዜ አለን። ነገር ግን ጊዜው ሲደርስ፣ የተከሰተው ነገር እኛ ካሰብነው በጣም የተለየ ነበር። ይህ በብዙ መልኩ ለአዲስ ኪዳን ደራሲዎች እውነት ነበር። በመጀመሪያው መቶ ዘመን ይኖሩ የነበሩት አብዛኞቹ አይሁዳውያን የእግዚአብሔር መንግሥት ድል እንዴት እንደሚመጣ አጥብቀው ይጠባበቁ ነበር። የጥንቶቹ የኢየሱስ ተከታዮች ግን እንዳሰቡት እንዳልሆነ ቀስ በቀስ አወቁ። ስለዚህ በተለያዩ መንገዶች፣ የአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት የመንግሥቱ ድል እንዴት እንደሚመጣ ለማስረዳት ያተኮረ ነበር።

የመንግሥቱ መምጣት በአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንዳሳደረ ለመረዳት፣ በመጀመሪያ የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣት የሚጠበቁትን ነገሮች እንዳስሳለን። ከዚያም የመንግሥቱን ሦስት እጥፍ ድል በምንለው ላይ የአዲስ ኪዳንን አመለካከት እንመለከታለን። በመጀመሪያ ከሚመጣው መንግሥት የሚጠበቁትን ነገሮች እናስብ።

## የሚጠበቁ ነገሮች

በመጀመሪያው መቶ ዘመን ዓ.ም, ሁሉም አይሁዳውያን ለአባቶቻቸው እምነት ትንሽም ቢሆን ቁርጠኝነት አድራጊው የእግዚአብሔር መንግሥት እንዲመጣ ጓጉተው ነበር። ሁሉም እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን ድል አድርጎ ሕዝቡን ለመንግሥቱ በረከት አሳልፎ እንደሚሰጥ ተስፋ አድርገው ነበር። ይህ ለኢየሱስ ተከታዮችም እውነት ነበር። ነገር ግን የእግዚአብሔር ድል አድራጊ መንግሥት ይመጣል ብለው እንዴት እና መቼ እንደሚጠብቁ አንዳንድ አስገራሚ ልዩነቶች ነበሩ።

በአንድ በኩል፣ ረቢዎች እና ሌሎች የእስራኤል መሪዎች የእግዚአብሔር መንግሥት የመጨረሻው ድል እንደሚመጣ ሲያስተምሩ፣ እንደ "የመጨረሻው ዘመን" እና "የጌታ ቀን" ያሉትን የብሉይ ኪዳንን የታወቁ ቃላት ጠቅሰዋል። ግን ስለ ሁለት ታላላቅ የታሪክ ዘመናትም ተናገሩ። ራቢዎች አሁን ያለውን የኃጢያት፣ የመከራ እና የሞት ዘመን "ይህ ዘመን" - ኦላም ሃዝ በዕብራይስጥ - እና ከምርኮ በኋላ የሚመጣውን የጽድቅ፣ የፍቅር፣ የደስታ እና የሰላም ዘመን "የሚመጣው ዘመን" - ኦላም ሃባ በዕብራይስጥ በማለት ብዙ ጊዜ ይጠቅሱታል።

"ይህ ዘመን" እስራኤላውያን ከተስፋይቱ ምድር በግዞት መውደቃቸው ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን አስተምረው ነበር። እርግጥ ነው፣ እግዚአብሔር በዚህ ዘመን ላይ ሉዓላዊ ነበር፣ እና ከጊዜ ወደ ጊዜ ንግሥናውን በሚያስደንቅ ሁኔታ ይገልጣል ወይም አሳይቷል። ነገር ግን በመጀመሪያው መቶ ዘመን ዓ.ም.፣ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ለብዙ መቶ ዓመታት ተጨቁነዋል እና ከእግዚአብሔር መንግሥት በረከቶች ተጠብቀው ነበር። ተስፋፍቶ የነበረው

*‘በሚመጣው ዘመን’ የእግዚአብሔር ጠላቶች ሙሉ በሙሉ እንደሚሸነፉና ከምድር ላይ እንደሚጠፉ ነበር። እናም የእግዚአብሔር ሰዎች ወደማይለካው የእግዚአብሔር ዓለም አቀፋዊ መንግሥት በረከቶች ለዘላለም እንደሚገቡ ነበር፡፡*




*በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ጽሑፎች እንዲሁም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ስንወያይ፣ አንዳንድ ጊዜ “ይህ ዘመን” እና “የሚመጣው ዘመን” የሚሉትን ቃላት እናገኛለን ወይም ያጋጥመናል። የእነዚህ ቃላት ትርጉም የሚከተለው ነው፦ “ይህ ዘመን” የሰው ልጅ የሚኖርበት ዘመን፣ ዘመን፣ ዘመን፣ ከውድቀት ወዲህ ያለው ዘመን ነው። በወደቀ ዓለም ውስጥ ሕይወት ነው. “የሚመጣው ዘመን” በብሉይ ኪዳን ነቢያት እንደተጠበቀው፣ እግዚአብሔር በተወሰነ መልኩ ገነትን የሚፈጥርበት ጊዜ ነበር። አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ይሆናሉ፣ እናም ድንጋይ የሆነው የሰው ልብ ይወገዳል፣ እናም ሁላችንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንከተላለን እና እናደርጋለን። በሰዎች መካከል ሁከት አይኖርም ነበር; በእንስሳት ዓለም ውስጥ እንኳን ምንም ዓይነት ጥቃት አይኖርም፡፡*

— *ዶክተር ኢካሃረደ ጄ ስቻናቤል*

በመጀመሪያው መቶ ዘመን የተለያዩ የአይሁድ ኑፋቄዎች ታሪክ “ከዚህ ዘመን” ወደ “መጪው ዘመን” ከመሸጋገሩ በፊት ምን መሆን እንዳለበት የተለያየ አመለካከት ነበራቸው። ነገር ግን አብዛኞቹ ወገኖች ከዚህ የሽንፈት ዘመን ወደ ድል አድራጊ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘመን የሚደረገው ሽግግር አስከፊ በሆነ ጦርነት እንደሚሆን ተስማምተዋል። የዳዊት ዙፋን ወራሽ የሆነው መሲሑ የሰማይ መላእክትንና የእግዚአብሔር ታማኝ ሕዝቦችን በእግዚአብሔር ሰብዓዊና መንፈሳዊ ጠላቶች ላይ ድል እንደሚያደርግ ያምኑ ነበር።

እግዚአብሔር የሰውን ጠላቶች ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ጠላቶችንም ያሸንፋል የሚለው እምነት በብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ይደገፍ ነበር። ለምሳሌ፣ በዘጸአት 12፡12 ላይ እግዚአብሔር ግብፃውያንን ብቻ ሳይሆን የግብፃውያንንም አማልክቶች ስለማሸነፍ ተናግሯል። በ1ኛ ሳሙኤል 5፡1-12 እግዚአብሔር ከፍልስጥኤማውያን ጋር ተዋጋ፣ እንዲሁም የሐሰት አምላካቸውን ዳጎንን ድል አደረገ። ኢሳይያስ 21:9 የባቢሎንን ሽንፈት ከባቢሎን አማልክቶች መጥፋት ጋር ያጣመረው ለዚህ ነው።

የብሉይ ኪዳን ምንባቦች እንደ ሐጌ 2፡6-9፤ ዘካርያስ 9–12 እና ሕዝቅኤል 38–39 በአይሁድ አፖካሊፕቲክ ጽሑፎች ውስጥ መሲሑ የእግዚአብሔርን ሠራዊት በመምራት አሕዛብን እና በእነርሱ ላይ የሚገዙትን እርኩሳን መናፍስትን ስለሚያሸንፍበት ታላቅ የጠፈር ጦርነት ትንቢቶች ተደርገው ተተርጉመዋል። በዚህ መንገድ መሲሑ የእግዚአብሔር ጠላቶች ሁሉ ድል ያደርጋል እንዲሁም ሁሉንም የእግዚአብሔር ሕዝቦች ወደ ክብር፣ ዓለም አቀፋዊ መንግሥቱ እንደሚያሳልፍ ይጠበቅ ነበር፡፡

በሌላ በኩል፣ እነዚህ አይሁዳውያን አመለካከቶች ተስፋፍተው እንደነበረው፣ የኢየሱስ ተከታዮች የእግዚአብሔርን መንግሥት የድል መምጣት አስቀድሞ መገመት ጀመሩ። እንደ ብዙዎቹ የዘመናቸው ሰዎች፣ የአዲስ ኪዳን ደራሲዎች ታሪክ በሁለት ታላላቅ ዘመናት እንደሚከፈል ያምኑ ነበር። መሲሑ የእግዚአብሔርን ሰብዓዊና መንፈሳዊ ጠላቶች እንደሚያሸንፍና የተዋጁትን የእግዚአብሔር ሕዝቦች “ከዚህ ዓለም” ወደ “መጪው ዘመን” በረከት እንደሚያወጣ ተስማምተዋል። የኢየሱስ ተከታዮች ግን ከዚህ ዘመን ወደ መጪው ዘመን የሚደረገው ሽግግር በዘመናቸው የነበሩት አብዛኞቹ አይሁዳውያን ካመኑት በተቃራኒ መንገድ እንደሚሆን አመኑ።

በመጀመሪያ ደረጃ፣ ከአብዛኞቹ አይሁዶች በተለየ፣ የአዲስ ኪዳን ደራሲዎች ኢየሱስ ተስፋ የተደረገበት መሲሕ፣ የዳዊት ልጅ፣ ለእግዚአብሔር መንግሥት የመጨረሻውን ዓለም አቀፍ ድል የሚያመጣ እንደሆነ ያምኑ ነበር። እናም ይህ ለኢየሱስ መሲህ የሆነው ቃል ኪዳን በአዲስ ኪዳን ውስጥ የፃፉትን ሁሉ በጥልቅ ቀርጿል።

ለኢየሱስ መሲሐዊ ንግሥና ያለውን ፍቅር አዲስ ኪዳን በሰጠው የንጉሣዊ ማዕረግ ውስጥ ማየት እንችላለን። ለምሳሌ፣ አዲስ ኪዳን ኢየሱስን 529 ጊዜ ያህል "ክርስቶስ" የሚል ንጉሣዊ ማዕረግ እንዳለው ይጠቅሳል። ክርስቶስ የሚለው የግሪክ ቃል የብሉይ ኪዳንን የዕብራይስጥ ቃል መሺያክን የተረጎመ ሲሆን ይህም መሢሕ የሚለውን ቃል ያገኘንበት ነው። በመጀመሪያ እነዚህ ቃላት በቀላሉ "የተቀባ" የሚል ፍቺ አላቸው። በብሉይ ኪዳን ዘመን፣ ነቢያት፣ ካህናት እና ነገሥታት በእስራኤል ልዩ የተቀቡ ሰዎች ነበሩ። ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ዘመን "የተቀባው" ወይም "መሲሑ" ወደ መጪው ዘመን ሽግግር ከሚያመጣው ከታላቁ የዳዊት ቤት ንጉሥ ጋር ተመሳሳይ ነበር ማለት ይቻላል።

በአዲስ ኪዳን ለኢየሱስ የተሰጠው ሁለተኛው የንጉሣዊ ማዕረግ "የእግዚአብሔር ልጅ" ነው። ይህ አገላለጽ ወይም እንደ "ወልድ" ወይም "የልዑል ልጅ" ያሉ አንዳንድ ልዩነቶች በአዲስ ኪዳን ውስጥ 118 ጊዜ ያህል ተጠቅሰዋል። ይህ አገላለጽ ኢየሱስ ትክክለኛ የእስራኤል ንጉሥ መሆኑን ያመለክታል። ናትናኤል ኢየሱስን ያለውን የዮሐንስ ወንጌል 1፡49 አድምጡ።

> ናትናኤልም መልሶ። መምህር ሆይ፥ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ፤ አንተ የእስራኤል ንጉሥ ነህ አለው። (ዮሐንስ 1:50).

ጴጥሮስም በማቴዎስ 16፡16 ላይ በኢየሱስ ላይ ያለውን እምነት ሲመሰክር፡-

> ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ። አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ። (ማቴዎስ 16:16).

ይህ አገላለጽ ኢየሱስ "የዳዊት ልጅ" ሲል ከተጠራበት ሦስተኛው ንጉሣዊ ስያሜ ጋር ተመሳሳይ ነው። ይህንንም በማቴዎስ፣ በማርቆስ እና በሉቃስ ወንጌሎች ውስጥ ኢየሱስን እንደ ትክክለኛ፣ እግዚአብሔር የሾመው የዳዊት ዙፋን ወራሽ እንደሆነ በመጥቀስ ቢያንስ 20 ጊዜ አይተነዋል።

ለምሳሌ በሉቃስ 1፡32-33 ላይ መልአኩ ገብርኤል ማርያምን ሲያናግራት እንዲህ ብሏታል።

> እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል፥ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤ በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘለላም ይነግሣል፥ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም። (ሉቃስ 1:32-33).

እዚህ ላይ ገብርኤል ስለ ኢየሱስ "የልዑል ልጅ" በሚል ንጉሣዊ ማዕረግ ተናግሯል። ከዚያም ኢየሱስ "በአባቱ በዳዊት ዙፋን ላይ" እንደሚቀመጥ ገለጸ። ሉቃስ ኢየሱስ "ለዘላለም እንደሚነግሥ መንግሥቱም ለዘላለም እንደማይጠፋ" ዘግቧል። የልዑል ልጅ እንደመሆኑ መጠን፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት የመጨረሻ፣ መጨረሻ የሌለውን ድል የሚያመጣው ኢየሱስ ነው።

እነዚህ ሁሉ ክፍሎች በአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት ውስጥ ያለውን ወሳኝ ትምህርት ያመለክታሉ፡ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት በሙላት ወደ ምድር የሚያመጣ መሲሕ ነው።


በሁለተኛ ደረጃ የጥንቶቹ የኢየሱስ ተከታዮች እነርሱም ሆኑ ሌሎች ባልጠበቁት መንገድ ከዚህ ዘመን ወደ መጪው ዘመን እንደሚሸጋገር ያምኑ ነበር።

በማቴዎስ 13፡31-32 ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚጠበቁ ለውጦችን የገለጠበትን መንገድ አድምጡ፡

ሌላ ምሳሌ አቀረበላቸው እንዲህም አለ። መንግሥተ ሰማያት ሰው ወስዶ በእርሻው የዘራትን የሰናፍጭ ቅንጣት ትመስላለች፤ እርስዋም ከዘር ሁሉ ታንሳለች፥ በአደገች ጊዜ ግን፥ ከአታክልቶች ትበልጣለች የሰማይም ወፎች መጥተው በቅርንጫፎችዋ እስኪሰፍሩ ድረስ ዛፍ ትሆናለች። (ማቴዎስ 13:31-32).

ኢየሱስ በዚህ ምሳሌ ላይ ድል አድራጊው የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ ትንሽ ነገር ማለትም "እንደ ሰናፍጭ ቅንጣት" ለተወሰነ ጊዜ እንደሚያድግና ከዚያም ወደ መጨረሻው እንደሚደርስ አስተምሯል።

የዘመናችን የሥነ መለኮት ሊቃውንት ብዙውን ጊዜ ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር መሲሐዊ መንግሥት መምጣት ያለውን አመለካከት "የተመረቀ የፍጻሜ ዘመን" ብለው ይጠሩታል። ይህ ሐረግ የሚያመለክተው የመሲሑ ሥራ በምድር ላይ አስቀድሞ መገለጡን ነው፣ ነገር ግን የመጨረሻው ድል ገና ይመጣል፡፡ እንዲሁም ስለ እርሱ "ቀድሞውኑ ግን ገና አይደለም" ብለው ይናገራሉ። በሌላ አነጋገር፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ድል አስቀድሞ መጥቷል፣ ነገር ግን እስካሁን በሙላት አልደረሰም። ይህ በሚመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት ድል ላይ ያለው አመለካከት ስለ አዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት ስፍር ቁጥር የሌላቸው ግንዛቤዎችን ይሰጣል።





የተመረቀ የመጨረሻ ዘመን

ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሲያውጅ ከእግዚአብሔር መንግሥት ጋር ከተያያዙት ትላልቅ ጥያቄዎች አንዱ፣ አሁን ያለ እውነት ነው? እርሱ በቃላቱ እና በተግባሩ ነው ወይንስ አሁንም የወደፊት አካል ነው? ምሑራን ስለ "የተመረቀው የእግዚአብሔር መንግሥት" ይናገራሉ። "የተመረቀው" ማለት የአሁንም ወደፊትም ነው ማለት ነው። ኢየሱስ መንግሥቱን ያውጃል። መንግሥቱ በቃሉና በተግባሩ በተለይም በመስቀል ሞትና በትንሳኤው እየደረሰች ነው። ስለዚህ መንግሥቱ ተመረቀ፣ ግን ገና አልተጠናቀቀም። ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ፣ ሙሉ በሙሉ ወደ ምድር ይመጣል፣ የተከበረውን ሰውነታችንን እንቀበላለን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ወደ ዘላለማዊ ግንኙነት እንገባለን። ስለዚህ አሁን ባለንበት ዘመን የምንኖረው በዘመኑ መካከል፣ በመንግሥቱ ምረቃ፣ ፍጻሜው መካከል ነው። አሁንም በእነዚህ አካላት ውስጥ እንኖራለን፤ አሁንም የምንኖረው በዚህ በወደቀው ዓለም ውስጥ ነው፣ነገር ግን መንግሥቱ መጥታለች ምክንያቱም ክርስቶስ በአብ ቀኝ እየገዛ ነው። እርሱ ደግሞ በልባችን ውስጥ እየገዛ ነው። እና ስለዚህ, መንግሥቱ መጥቷል, "ቀድሞውንም" ነው, ግን አሁንም ወደፊት ነው. እንዲሁም "ገና" ነው፡፡

— ዶክተር ማርክ ኤል ስትራውስ

በአጠቃላይ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣት የአዲስ ኪዳንን አመለካከት እንደ ሦስት እጥፍ ድል አድርጎ ማሰብ ይረዳል። በመጀመሪያ በምርቃቱ፣ እግዚአብሔር በኢየሱስ ሕይወት፣ ሞት፣ ትንሣኤ እና ዕርገት እና በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን በሐዋርያት እና በነቢያቱ የመሠረት አገልግሎቶች የመንግሥቱን ድል አስጀምሯል። ከዚህ በኋላ፣ በመቀጠል፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ድል ከሰማይ ዙፋኑ አስነሳ። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ኢየሱስ መንግሥቱን ማስፋፋቱን ይቀጥላል። በመጨረሻም ኢየሱስ በክብር ሲመለስ የመንግሥቱን ፍጻሜ ያመጣል። ይህ ክፋት ሁሉ ሲጠፋ እና የእግዚአብሔር ክብር ያለው መንግስት በዓለም ውስጥ በሚዘረጋበት ጊዜ የእግዚአብሔር መንግስት የመጨረሻው ድል ነው።





የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣት ሦስት እጥፍ ድል ነው።

የአዲስ ኪዳን ደራሲዎች የተለያዩ ስነ-መለኮታዊ ጉዳዮችን ለማብራራት ራሳቸውን እንደሰጡ፣ ይህን ያደረጉት በኢየሱስ መሲሃዊ ስራ ሶስት እርከኖች ውስጥ ነው።

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው፣ የመንግሥቱ መምጣት በመጀመሪያው መቶ ዘመን የነበሩት የኢየሱስ ተከታዮች ይጠብቋቸው የነበሩትን ነገሮች ቀይሯል። አሁን፣ በአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት ውስጥ የተካሄደውን የሶስት እጥፍ የእግዚአብሔር መንግሥት ድል ወሳኝ ቦታን እንመልከት።

## የሦስት ገጽታዎች ድል

የእግዚአብሔር መንግሥት ድል የሚመጣው በኢየሱስ መሲሐዊ ሥራ ምረቃ፣ ቀጣይነት እና ፍጻሜ ላይ መሆኑ በቀደመችው ቤተክርስቲያን ውስጥ ሁሉንም ዓይነት ጥያቄዎች አስነስቷል። ኢየሱስ አስቀድሞ ምን አከናውኗል? በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ምን ያከናውናል? ሲመለስ ምን ያደርጋል? እነዚህ አይነት ጥያቄዎች በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን በጣም አስፈላጊ ከመሆናቸው የተነሳ የአዲስ ኪዳንን ሥነ-መለኮት በጥልቅ ቀርፀዋል። የአዲስ ኪዳን ደራሲዎች የእግዚአብሔር ጠላቶች ሽንፈት እና የእግዚአብሔር ሕዝብ ነጻ መውጣት የጀመረው በክርስቶስ የመጀመሪያ ምጽዓት መሆኑን ነው። እነዚህ ክስተቶች በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ይቀጥላሉ፣ እና በመጨረሻ በክርስቶስ ሁለተኛ የድል ምጽአት ፍጻሜ ላይ ይደርሳሉ።




የመንግሥቱ ሦስት ደረጃዎች

ይህ ሦስት ጊዜ ድል የአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮትን የቀረጸባቸውን አንዳንድ መንገዶች ለመጠቆም ጊዜ ብቻ ይፈቅድልናል፣ ነገር ግን በሁለት አቅጣጫ ለማየት ይጠቅመናል። በመጀመሪያ አዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ጠላቶች በመንግሥቱ ሦስት እርከኖች የተሸነፉትን እንዴት እንደሚያብራራ እናስተውላለን። ከዚያም በሦስቱም ደረጃዎች ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ መዳን የአዲስ ኪዳን ትምህርቶችን እንመረምራለን። አስቀድመን የእግዚአብሔርን ጠላቶች ሽንፈት እንመልከት።

### ሽንፈት

የማያምኑት አይሁዳውያን መሲሑ የእግዚአብሔርን ሰብዓዊም ሆነ መንፈሳዊ ጠላቶች እንደሚያሸንፍ ያምኑ ነበር። የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎችም ይህንን ያምኑ ነበር። ነገር ግን ኢየሱስ ይህን የሚያደርገው ለእያንዳንዱ የመንግሥቱ ደረጃ በሚስማማ መንገድ እንደሆነም ተረድተዋል። የአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት አጽንዖት የሚሰጠው የኢየሱስ ስልት በመንግሥቱ ምረቃ ላይ ሁለት ጊዜ ነበር። በአንድ በኩል፣ በእግዚአብሔር መንፈሳዊ ጠላቶች ላይ የአምላክን ፍርድ አወረደ። በአገልግሎቱ በሙሉ፣ ኢየሱስ እርኩሳን መናፍስትን ከስልጣን ቦታቸው በማባረር ሃይላቸውን አሳጣቸው። በሌላ በኩል ግን ለእግዚአብሔር ሰብዓዊ ጠላቶች የእግዚአብሔርን ምሕረት አሳይቷል። በእርግጠኝነት፣ ክርስቶስ

ለሰዎች ያለው ምሕረት ብዙ በረከቶችን አስገኝቶላቸዋል፣ ነገር ግን እርኩሳን መናፍስትን ሰብዓዊ አገልጋዮቻቸውን በመዝረፍ ሽንፈትን አበረታቷል።


ምረቃ

በማቴዎስ 12፡28-29፣ ኢየሱስ ራሱ ይህንን ስልት ሲናገር እንዲህ ሲል ገልጿል:

እኔ ግን በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ፥ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ደርሳለች። ወይስ ሰው አስቀድሞ ኃይለኛውን ሳያስር ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ እቃውን ሊነጥቀው እንዴት ይችላል? ከዚያም ወዲያ ቤቱን ይበዘብዛል። (ማቴዎስ 12:28-29).

ኢየሱስ መጥቶ 'ቤቱን ሊዘርፍ' ሲል አጋንንትን አሰረ ወይም "ኃይለኛውን ሰው አስሮ" ነው። በሌላ አነጋገር፣ ኢየሱስ አጋንንትን አውጥቶ በአጋንንት ቁጥጥር ሥር ያሉትን ነፃ አውጥቷል።

ይህንን ባለሁለት ስልት ኢየሱስ በተናገረበት እንደ ዮሐንስ 12፡31-32 ባሉ ቦታዎች ላይ ማየት እንችላለን:

አሁን የዚህ ዓለም ፍርድ ደርሶአል፤ አሁን የዚህ ዓለም ገዥ ወደ ውጭ ይጣላል፤ እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደ ሆነ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ። (ዮሐንስ 12:31-32).

አሁንም፣ በመንግሥቱ ምረቃ ወቅት፣ ኢየሱስ ክፉ መናፍስትን ወይም "የዚህ ዓለም ገዥ በሆነው በሰይጣን" ላይ በቀጥታ ጥቃት ሰነዘረ። አባረረው እና አቅሙን አሳጣው። ነገር ግን ከዚህ በሰይጣን ላይ ከሚሰነዘረው ጥቃት ጋር፣ ኢየሱስ ለሰው ልጆች መዳንን ሰጥቷል።

> አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ይገረማሉ፣ ይህ የክርስቶስ ቪክቶር፣ የድል አድራጊው ክርስቶስ አመለካከት፣ ክርስቶስ ለኃጢአታችን የሞተው፣ ምትክ የሆነ የኃጢያት ክፍያ ነው ከሚለው ሃሳብ ጋር እንዴት ወጥነት ያለው ወይም ተዛማጅ ሊሆን ይችላል? … በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ፣ ኢየሱስ ለሦስተኛ ጊዜ የሰው ልጅ እባቡ በምድረ በዳ እንደተሰቀለ ሲናገር - ዮሐንስ 12 ላይ ነው - ያንን መነሳት በተለይ "አሁን የዚህ ዓለም ገዥ ይሆናል" ከሚለው መግለጫ ጋር አገናኘው። ወደ ታች መጣል" ስለዚህ፣ ኢየሱስ የተረገመውን እባብ ቦታ ወሰደ፣ ሞትን ከውስጥ ለማጥፋት ወደ ሞት ሄደ። ስለዚህ፣ እንደ ክርስቶስ ቪክቶር የመጀመሪያ ስራው በመስቀል ላይ በመሰቀል ሞትን ከውስጥ ማጥፋት ነው።
>
> — ቄስ ሚካኤል ጄ.ግሎዶ

የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ጠላቶች ሽንፈት ለክርስቶስ የመከፈቻ ስራ በጣም አስፈላጊ ነበር፡፡ ስለዚህም እንደ ዕብራውያን 2፡14-15 ባሉት ምንባቦች ውስጥ፣ የአዲስ ኪዳን ፀሐፊዎች ስለ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ስላደረገው የስርየት ሞት ከዚሁ ሁለት ስልት አንፃር ጽፈዋል። ኢየሱስ በሞቱ ሰይጣን በሰው ልጆች ላይ ያለውን ስልጣን እንደፈረሰ ግልጽ አድርገዋል። ኢየሱስ የሰው ልጆችን ኃጢአት በማስተሰረይ የኃጢአትና የሞት ባሪያዎች የነበሩትን ሰዎች ነፃ አውጥቷቸዋል።

ሐዋርያው ጳውሎስ በጻፈበት በቆላስይስ 2፡15 ላይ እነዚህ ሐሳቦች በግልጽ ይታያሉ።

አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ፥ ድል በመንሣት በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው። (ቆስይስ

2:15).


ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞት ህዝቡን ከኃጢአት አገዛዝ ነፃ ባወጣ ጊዜ የአጋንንት ኃይሎች እና ባለ ሥልጣናት የታወቁበትን ቦታ አጥተዋል።

ከዚህ አንፃር፣ በኤፌሶን 4፡8 ላይ የክርስቶስ ትንሣኤና ዕርገት የሰይጣን ሰብዓዊ አገልጋዮችን መዘረፉ መገለጹ ሊያስደንቅ አይገባም።

ስለዚህ። ወደ ላይ በወጣ ጊዜ ምርኮን ማረከ ለሰዎችም ስጦታን ሰጠ ይላል። (ኤፌሶን 4:8).

ይህ ክፍል እንደሚያመለክተው፣ ወንዶችና ሴቶች በክርስቶስ ወደ ማመን ሲመጡ፣ ክርስቶስ ከሰይጣን መንግሥት እንደዘረፋቸው ያሀል ነው።

ይህ የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ተቃዋሚዎችን ለማሸነፍ የሚያስችል ስልት በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ የክርስቶስ ሐዋርያት ባደረጉት የመክፈቻ ሥራ ላይም ይገኛል። የኢየሱስን ምሳሌ በመከተል በአህዛብ ሕዝቦች ውስጥ ወንጌልን ሲሰብኩ አጋንንትን ሲያወጡና የበርካታ ሰብዓዊ አገልጋዮችን ሰይጣንን ሲያባርሩ ሐዋርያት ደጋግመው አጋንንትን ያስወጡ ነበር።


ቀጣይነት

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የክርስቶስን መንግሥት ቀጣይነት ስናጤን፣ የክርስቶስ ተከታዮች ኢየሱስ በምርቃቱ ወቅት የተጠቀመበትን ስልት መከተላቸውን ማስተዋላችን የሚያስገርም አይደለም። በእግዚአብሔር ሰብዓዊ ጠላቶች ላይ ድል ከማግኘት ይልቅ ትኩረታችንን የእግዚአብሔርን መንገዶች በሚቃወሙ ክፉ መናፍስት ላይ ማተኮር አለብን።

ምንም እንኳን ብዙ የዘመናችን ክርስቲያኖች ሊገነዘቡት ባይችሉም፣ የአዲስ ኪዳን መንግሥት ሥነ-መለኮት ደጋግሞ ያሳስበናል የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ከሰዎች ጋር ሳይሆን ከሰይጣንና ከሌሎች እርኩሳን መናፍስት ጋር ትጣላለች። እናም ከእነዚህ የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ጠላቶች ጋር መታገል የእኛ ኃላፊነት ነው።

ለዚህ ነው፣ በኤፌሶን 6፡11-12 ባሉት ክፍሎች፣ አዲስ ኪዳን ችግሮቻችንን እና ትግላችንን ከክፉ መናፍስት ጋር ግጭት አድርጎ የሚተረጉመው። እንዲህ ይላል፡

የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ። መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ። (ኤፌሶን 6:11-12).

ብዙ ጊዜ የዘመናችን ክርስቲያኖች የሕይወታቸውን ተጋድሎ ከሰዎች ጋር ግጭት አድርገው ያስባሉ። እዚህ ላይ ግን ቤተ ክርስቲያንን የምትጋፈጠው ግጭት “ከዲያብሎስ” “ከገዥዎች” “ከሥልጣናት” “ከዚህ የጨለማ ዓለም ኃይሎች” እና “በሰማያዊው ዓለም ካሉት የክፉ መንፈሳዊ ኃይሎች” ጋር መሆኑን እናያለን። የእግዚአብሔርን ሙሉ የጦር ትጥቅ በመልበስ እነዚህን የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚቃወሙ መንፈሳውያንን ሥልጣናቸውን ልናሳጣቸው እንችላለን።

ይህ ክፍል በክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የክርስቶስን መንግሥት ገጽታ አድርጎ በመንፈሳዊ ጦርነት ላይ አጽንዖት በመስጠት የተለመደ ነው። ከሰይጣንና ከሌሎች እርኩሳን መናፍስት ጋር የምንገጥመው የማያቋርጥ ግጭት እንደ ኤፌሶን 4፡27፤ ሌሎች በርካታ ምንባቦች ውስጥም ይገኛል። 1 ጢሞቴዎስ 3:7; 2 ጢሞቴዎስ 2:26; ያእቆብ 4:7;

1 ጴጥሮስ 5:8; 1 ዮሐንስ 3:8; እና ይሁዳ 9:: ነገር ግን በተመሳሳይ ጊዜ፣ በ2ኛ ቆሮንቶስ 5፡20 ላይ እንደምናነበው፣ የእግዚአብሔርን ምሕረት ለሰብዓዊ ጠላቶቹም መዘርጋት አለብን።

> እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን። (2 ቆሮንቶስ 5:20).

የጳውሎስን ምሳሌ በመከተል የእግዚአብሔር መንግሥት ተወካዮች እንደመሆናችን መጠን 'የክርስቶስ አምባሳደሮች' እንደመሆናችን መጠን በእግዚአብሔር እና በሰብዓዊ ጠላቶቹ መካከል እርቅ እንዲፈጠር በመፈለግ የእግዚአብሔርን መንፈሳዊ ጠላቶች ማሸነፋችንን እንቀጥላለን።



ፍጻሜ

የአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት ደግሞ የእግዚአብሔርን ጠላቶች ሽንፈት ከክርስቶስ መንግሥት ፍጻሜ ጋር ያዛምዳል። ይሁን እንጂ በፍጻሜው ወቅት በኢየሱስ ስትራቴጂ ውስጥ አስደናቂ ለውጥ እንደሚመጣ ልብ ማለት ያስፈልጋል። ክርስቶስ ተመልሶ ሲመጣ ለእግዚአብሔር ለሰብዓዊ ጠላቶች ምሕረትን አይሰጥም። ይልቁንም ክርስቶስ ፍጹም ሽንፈታቸውን፣ ከምድር መጥፋት እና የዘላለም ፍርድ ለማምጣት ከእግዚአብሔር መንፈሳዊ እና ሰብዓዊ ጠላቶች ጋር በጦርነት ይመራል።

ራእይ 19:13-15 የእግዚአብሔር ሰብዓዊ ጠላቶች በፍጻሜው ወቅት የተሸነፉበትን መንገድ የሚገልጽበትን መንገድ አድምጡ፡

> በደምም የተረጨ ልብስ ተጐናጽፎአል፥ ስሙም የእግዚአብሔር ቃል ተብሎአል።በሰማይም ያሉት ጭፍራዎች ነጭና ጥሩ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ ለብሰው በአምባላዮች ፈረሶች ተቀምጠው ይከተሉት ነበር። አሕዛብንም ይመታበት ዘንድ ስለታም ሰይፍ ከአፉ ይወጣል፤ እርሱም በብረት በትር ይገዛቸዋል፤ እርሱም ሁሉን የሚገዛ የእግዚአብሔርን የብርቱ ቍጣውን ወይን መጥመቂያ ይረግጣል። (ራእይ 19:13-15).

በተመሳሳይ መልኩ፣ ራዕይ 20፡10 የክርስቶስን በክብር መመለስ በክፉ መናፍስት እና በሰይጣን ላይ የመጨረሻ የፍርድ ጊዜ እንደሆነ ያሳያል፡-

> ያሳታቸውም ዲያብሎስ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሣቀያሉ። (ራእይ 20:10).

እርግጥ ነው፣ እነዚህን ጉዳዮች በአጭሩ ብቻ ነው ያቀረብነው። ነገር ግን ከእነዚህ ምሳሌዎች የአዲስ ኪዳን ደራሲዎች ይህንን የመንግሥቱን የድል ገጽታ ደጋግመው ማብራራት አስፈላጊ እንደሆነ ተሰምቷቸው እንደነበር ማየት እንችላለን። በክፉ መናፍስት ላይ የሚደረገውን ጥቃት ቅድሚያ አጽንኦት ሰጥተው ነበር፤ እናም ለእግዚአብሔር ሰብዓዊ ጠላቶች ያለውን ደግነት በመንግሥቱ ምረቃ እና ቀጣይነት ላይ አፅንዖት ሰጥተዋል። ነገር ግን በመጨረሻ፣ ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ፣ ሁለቱም ሰዎች እና መንፈሳዊ ጠላቶች በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ፍርድ ስር እንደሚመጡም ጠቁመዋል። እነዚህ አጽንዖቶች የእግዚአብሔር ጠላቶች ሽንፈት የአዲስ ኪዳን መንግሥት ሥነ-መለኮት ወሳኝ ገፅታ መሆኑን ያረጋግጣሉ።

> *መንግሥቱ ተጀምሯል፣ እዚህ ነው፣ ግን አሁንም መንገዱን እየዘረ፣ እስከ ፍጻሜው ድረስ መንገዱን እየሠራ ነው። ታዲያ ኢየሱስ በጠላቶቹ ላይ ድል ተቀዳጅቷል የሚለው ጥያቄ የሚጠይቀው በየትኞቹ መንገዶች ነው? እንግዲህ፣ ከሁሉ አስቀድሞ፣ ሰይጣንን ድል ያደርግ ዘንድ ወሳኙ ድል*

> በራሱ በመስቀሉ ላይ ነው።...በዚህም መልኩ ወሳኙ ጦርነት ተካፍሏል እና አሸንፏል። ለዚህም ነው ለምሳሌ በራዕይ 12 ላይ ቅዱሳን ለወንድሞች ከሳሽ ምላሽ ሰጡ፤ በበጉ ደም አሸንፈዋል፡፡ ሰይጣንን ድል ነሡት - በምሳሌያዊ አነጋገር በራዕይ 12 ተገልጿል - በበጉ ደም አሸንፈዋል። እናም፣ ያን ጦርነቱ አስቀድሞ አሸንፏል። ነገር ግን እንደ ሂትለር በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ ላይ ጦርነቱ ማብቃቱን ሲመለከት አላቆመም. ጊዜው አጭር መሆኑን ስለሚያውቅ በንዴት ተሞላ። ስለ ሰይጣን የተነገረው ይህ ነው። ስለዚህ ሰይጣን አሁን የበለጠ ጨካኝ ነው፣ እናም ወንጌል በገፋ ቁጥር ብዙ ሰዎች ይለወጣሉ፣ ፅድቅ በግለሰብ ህይወት፣ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፣ በማንኛውም አይነት ንዑስ ባህሎች ውስጥ ይመሰረታል፣ ይህ አስቀድሞ የሰይጣን እና የእነዚያ ጨለማን የሚወዱ ሁሉ ቀጣይነት ያለው ሽንፈት ነው። የፍጻሜው ድል የመጨረሻ አቅጣጫ ደግሞ የዚህ ዓለም መንግስታት የአምላካችንና የክርስቶስ መንግስታት ሲሆኑ ለዘላለምም ይነግሣል… ነጥቡም አቅጣጫው መቀመጡ ነው ፊልጵስዩስ 2 እንዳስቀመጠው። ጉልበት ሁሉ ይንበረከካል፣ ምላስም ሁሉ ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክራል፣ እናም ዋናው ድል ተቀዳጅቷል። ያ አሁንም በአንዳንድ ሁኔታዎች መሠራት አለበት። በደስታ፣ በመንፈስ ኃይል፣ ጉልበታቸውን በሚያጎነብሱ በብዙዎች ህይወት ውስጥ እየተሰራ ነው። ግን በመጨረሻው ቀን ሁሉም ሰው ጉልበቱ ይንበረከካል።
>
> — ዶክተር ዲ.ኤ. ካርሰን

የእግዚአብሔር መንግሥት ሦስት እጥፍ ድል የእግዚአብሔርን ጠላቶች ሽንፈት እንዴት እንደሚጨምር ከተመለከትን፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነፃ መውጣቱ በአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት ውስጥ ትልቅ ሚና እንዴት እንደሚጫወት ልንጠቁም ይገባል።

### አርነት መውጣት

ለአብዛኞቹ አንባቢዎች ጎልቶ የሚታየው የመንግሥቱ ምረቃ አንድ ገጽታ ካለ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ መንግሥቱ በረከቶች መውጣቱ ነው። ለምሳሌ፣ ወንጌሎች በኢየሱስ ተአምራት ላይ ትኩረት ካደረጉባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች አንዱ እነዚህ ተአምራት ኢየሱስ ወደ ምድር ያመጣውን የመንግሥቱን በረከቶች የሚወክሉ በመሆናቸው ነው። የኢየሱስ ተአምራት የእግዚአብሔር ሕዝቦች በሚመጣው ዓለም ለዘላለም የሚያገኙት የመንግሥት በረከቶች ጊዜያዊ ግምቶች ነበሩ። ከዚህም ባሻገር፣ ኢየሱስ ለድሆች፣ ለችግረኞች እና በሌሎች መከራ ለሚደርስባቸው ማኅበራዊ ፍትህ የሰጠው ትኩረት የመንግሥቱን ጠቃሚ በረከቶች ያመለክታል።

የኢየሱስ እና የሐዋርያቱ እና የነቢያቱ ተአምራት እና ማህበራዊ ፍትህ አስደናቂ የሆኑ በረከቶች ነበሩ። ነገር ግን በእግዚአብሔር መንግሥት ምርቃት ውስጥ ትልቁ በረከት ክርስቶስ በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ የሰጣቸው የዘላለም ድነት ስጦታ ነው።

ለዚህም ነው በቆላስይስ 1፡13-14 ጳውሎስ በክርስቶስ መዳንን መቀበል ከአንዱ መንግሥት ወደ ሌላው መንግሥት ነጻ መውጣቱን የገለጸው።



ቪዲዮዎችን፣ የትምህርት መመሪያዎችና ሌሎች ግብዓቶችን ለማግኘት Thirdmill at thirdmill.org. ይመልከቱ



ምረቃ

እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፥ ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን። (ቆላይስ 1:13-14).

ወደ መንግሥት በረከቶች ነፃ መውጣቱ ጭብጥ አዲስ ኪዳን የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ለምን እንደሚያጎላም እንድንረዳ ይረዳናል። በሐዋርያዊው አገልግሎት መጨረሻ፣ በክርስቶስ ተከታዮች ላይ የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ለእያንዳንዱ አማኝ የተሰጠ የመጪው ዓለም አንድ በረከት ነው። በ2ኛ ቆሮንቶስ 1፡21-22 እንደምናነበው፡-

በክርስቶስም ከእናንተ ጋር የሚያጸናንና የቀባን እግዚአብሔር ነው፥ ደግሞም ያተመን የመንፈሱንም መያዣ በልባችን የሰጠን እርሱ ነው። (2 ቆሮንቶስ 1:21-22).


ይህ ምንባብ ከኤፌሶን 1፡14 ጋር ትይዩ ነው። ሁለቱም ክፍሎች መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስ "በእኛ ላይ የባለቤትነት ማኅተም" መሆኑን ያመለክታሉ። እርሱ "ለመጣው ነገር ዋስትና የሚሰጥ ተቀማጭ ገንዘብ" ነው። በሌላ አነጋገር፣ ዛሬ በሕይወታችን ያለው የእግዚአብሔር ኃይል የሆነው መንፈስ ቅዱስ፣ ክርስቶስ በክብር በሚመለስበት ጊዜ የክርስቶስ ተከታዮች የሚያገኙት የታላቁ ርስት የመጀመሪያ ክፍል ነው።

አዲስ ኪዳን በክርስቶስ መንግሥት ቀጣይነት ጊዜ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ነፃ መውጣቱንም ይናገራል። በቤተክርስቲያን ቀጣይነት ባለው ህይወት፣ የአዲስ ኪዳን ደራሲዎች የክርስቶስ ተከታዮች እግዚአብሔር እንዴት ለመንግስቱ በረከቶች እንዳዳናቸው እንዲያስታውሱ አበረታቷቸዋል። የአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት አጽንዖት የሚሰጠው፣ እግዚአብሔር ስለ ኃጢአታችን ከፍርድ አዳነን ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ለቤተክርስቲያኑ መስጠቱን ይቀጥላል። ለምሳሌ 1ኛ ቆሮንቶስ 4፡20ን አድምጡ፡

የእግዚአብሔር መንግሥት በኃይል ነው እንጂ በቃል አይደለምና። (1 ቆሮንቶስ 4:20).

እዚህ፣ እንደሌሎች ብዙ ቦታዎች፣ ጳውሎስ በአእምሮው የነበረው "ኃይል" የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው።

የእግዚአብሔር መንፈስ ከቀን ወደ ቀን የምንለማመደው ለህዝቡ የእግዚአብሔር በረከቶች አስደናቂ እውነታ ነው። እርሱ ይቀድሰናል፣ ፍሬውን በሕይወታችን ያፈራል፣ በደስታ ይሞላናል፣ በጠላቶቻችን ላይ በኃይሉ ያበረታናል። ምንም እንኳን ዛሬ ብዙ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ቅርንጫፎች መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ህይወት ውስጥ ያለውን ሚና አፅንዖት ባይሰጡም፣ እርሱ በክርስቶስ መንግስት ቀጣይነት ጊዜ ታላቁ በረከታችን ነው።


ቀጣይነት

የአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት እንዲሁ በመንግሥቱ ቀጣይነት የሚኖሩ የክርስቶስ ተከታዮች ተስፋቸውን በሚመጣው መንግሥት በረከቶች ላይ እንዲያተኩሩ ያበረታታል። ዕብራውያን 12:28 የክርስቶስ ተከታዮች ከፊታቸው ካሉት የመንግስት በረከቶች አንጻር ታማኝ ሆነው እንዲቀጥሉ ጥሪ ያቀርባል:

> ስለዚህ የማይናወጥን መንግሥት ስለምንቀበል በማክበርና በፍርሃት እግዚአብሔርን ደስ እያሰኘን የምናመልክበትን ጸጋ እንያዝ፤ (ዕብራውያን 12:28).

በያዕቆብ 2:5 ላይ ደግሞ እንዲህ እናነባለን።

> የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ስሙ፤ እግዚአብሔር በእምነት ባለ ጠጎች እንዲሆኑ ለሚወዱትም ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን መንግሥት እንዲወርሱ የዚህን ዓለም ድሆች አልመረጠምን? (ያዕቆብ 2:5).

ያዕቆብ መንግሥቱን የሚቀበሉት ባለጠጎች ስላልሆኑ ቤተ ክርስቲያን ለሀብታሞች ማድላት እንድታቆም አሳስቧል። ከዚህ ይልቅ “በእምነት ባለ ጠጎች” እና “የሚወዱትን” “የተስፋውን መንግሥት ይወርሳሉ።

ኢየሱስ መንግሥቱን በመረቀ ጊዜ ሕዝቡን ወደ መንግሥት በረከቶች አሳልፏል። የመንግሥቱ በረከቶችም በቤተ ክርስቲያን ሕይወት በታሪክ ቀጥለዋል። ነገር ግን የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በረከቶች ነፃ መውጣቱ የመንግሥቱ የመጨረሻ ፍጻሜ ድረስ እንደማይፈጸም ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተምራሉ። በፍጻሜው ላይ፣ የእግዚአብሔር ሰዎች የመንግሥቱን ተስፋ የተጣለባቸውን በረከቶች ሙሉ በሙሉ ያገኛሉ። በራዕይ 11:15 ላይ እንደምናነበው:

> ሰባተኛው መልአክ ነፋ፤ በሰማይም። የዓለም መንግሥት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣል (ራእይ 11:15).

ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ፣ የአለም መንግስት ሙሉ በሙሉ በድል አድራጊው የእግዚአብሔር መንግስት ይተካል። በራዕይ 5:9-10 ላይ የሰማይ ፍጡራን የክርስቶስን ውዳሴ የሚዘምሩበትን አድምጡ።

> መጽሐፉን ትወስድ ዘንድ ማኅተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃል፥ ታርደሃልና፥ በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው፥ በምድርም ላይ ይነግሣሉ እያሉ አዲስን ቅኔ ይዘምራሉ። (ራእይ 5:9-10).

በፍጻሜው ላይ፣ የእግዚአብሔር ሕዝቦች “የካህናት መንግሥት” እና “በምድር ላይ ይነግሳሉ” እንዲሆኑ ነፃ ይሆናሉ።

> ስለ ኢየሱስ ዳግመኛ መምጣት እና የመጨረሻውን ድል ስለመቀዳጀት ስናስብ፣ ኢየሱስ ጠላቶቹን በማሸነፍ ፈረንሣይኛ በጥሬው የኃይል አጠቃቀምን ብቻ በሚሉት ነገር ጠላቶቹን እንደሚያሸንፍ ማሰብ አንፈልግም። በራዕይ ውስጥ ከኢየሱስ አፍ ስለሚወጣው ሰይፍ ይናገራል፣ እናም የቃሉ ሰይፍ፣ የፍትህ ሰይፍ፣ የመጨረሻው ፍርድ እንደማንኛውም ነገር መጋለጥ ነው። እና እንደዚሁም፣ ለቅዱሳን በተለይም በአዲስ ኪዳን አውድ፣ መጽደቅ ከዋና መሪ ሃሳቦች አንዱ ነው። በኢየሱስ ማመን ቀጥለዋል እና ሌላውን ጉንጭ በማዞር ጠላቶቻችሁን መውደድ እና እነዚህን ሁሉ ሌሎች ድርጊቶች ሲያደርጉ ዓለም ይህ ፍጹም ሞኝነት ነው ይላል። ስለዚህ, በፍርድ ጊዜ, ሁሉም ነገር ግልጽ ይሆናል, ሁሉም ነገር ግልጽ ይሆናል; እውነት ይወጣል ይህም ለቅዱሳን የምስራች ሲሆን ለክፉዎች ደግሞ ክፋታቸው ኢየሱስንና መልእክቱን በመቃወም ላይ ያተኮረ ስለነበር መጥፎ ዜና


ፍጻሜ

ነው፡፡

— ዶክተር ሾን ማክዶን

እንደምናየው፣ የአዲስ ኪዳን ደራሲዎች ትኩረታቸውን ወደ እግዚአብሔር ጠላቶች ሽንፈት እና ሕዝቡን ወደ መንግሥት በረከቶች መዳን በኢየሱስ መሲሐዊ ሥራ ደረጃ ላይ ነበር። እነዚህ አካላት መጀመሪያ ላይ ግንኙነታቸው የተቋረጠ ቢመስልም፣ በአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት ውስጥ አንድ ላይ ተጣምረው አጽንዖት ተሰጥቶባቸዋል ምክንያቱም እነርሱ ወሳኝ ጭብጥን ይወክላሉ- የእግዚአብሔር መንግሥት በክርስቶስ የድል መምጣት።

## ማጠቃለያ

በዚህ ትምህርት፣ በአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት ውስጥ የእግዚአብሔርን መንግሥት አስፈላጊነት ተመልክተናል። የአዲስ ኪዳን ትንሽ ወይም የተገፋ ትምህርት ከመሆን ይልቅ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት የአዲስ ኪዳን ደራሲያን ያስተማሩት ትምህርት እምብርት ነው። ይህ እንዴት እውነት እንደሆነ ከመንግሥቱ ምሥራች ጋር መርምረናል። እንዲሁም የአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት በክርስቶስ መንግሥት ምርቃት፣ ቀጣይነት እና ፍጻሜ ላይ በመንግሥቱ መምጣት ላይ እንዴት እንዳተኮረ አይተናል።

እንደተመለከትነው፣ የአዲስ ኪዳን እምነት ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። የአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት ለእግዚአብሔር መንግሥት የድልን የምሥራች እና ይህ ድል በክርስቶስ መንግሥት ሦስት እርከኖች እንዴት እንደመጣ፣ እየመጣ እና እንደሚመጣ አጽንዖት ይሰጣል። እነዚህ መሠረታዊ የመንግሥት ጽንሰ-ሐሳቦች አንዳንድ በጣም አስፈላጊ የሆኑትን የአዲስ ኪዳን ጭብጦች ያመለክታሉ። እነርሱን ማስታወስ ስለ አዲስ ኪዳን ስነ-መለኮት ያለንን ግንዛቤ በእጅጉ ያሳድጋል። እና በአዲስ ኪዳን ትምህርቶች ውስጥ አዲስ ትርጉምን እናገኛለን። በክርስቶስ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር መንግሥት ጭብጥ ሁሉንም የአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት ገጽታዎች ያጠቃልለ ነው፡፡

# አስተዋጽኦ ያደረጉ ጸሐፊዎች

**ዶ/ር ሲሞን ቫይበርት (አስተናጋጅ)** የኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ የዊክሊፍ አዳራሽ ምክትል ርዕሰ መምህር ሲሆኑ የስብከት ትምህርት ቤት ዳይሬክተር ሆነው ያገለግላሉ። ዶክተር ቫይበርት የቲኤች ኤም ከግላስጎው ዩኒቨርሲቲ፣ ዲ.ሚን. ከተሃድሶ ቲዎሎጂካል ሴሚናሪ፣ እና በከፍተኛ ትምህርት በመማር እና በማስተማር የድህረ ምረቃ ዲፕሎማ ከኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ አግኝተዋል። እርሳቸው የላቲመር ትረስት ባለአደራ፣ የእንግሊዝ ቤተክርስቲያን ወንጌላውያን ምክር ቤት አባል እና የቃል እና የመንፈስ ህብረት ሊቀመንበር ሆነው አገልግለዋል። ዶ/ር ቫይበርትም የቅዱስ ሉክ ቤተክርስቲያን የዊምብልደን ፓርክ ቪካር በመሆን ለ8 ዓመታት አገልግለዋል። የስብከት ልቀት፡ ከምርጥ መማር (IVP, 2011) ጨምሮ በርካታ መጽሃፎችን እና ሥነ-መለኮታዊ ጽሑፎችን አዘጋጅቷል። ውጥረት፡ የሰላም መንገድ (ኢንተር-ቫርሲቲ ፕሬስ፣ 2014); እና ኢየሱስ የለወጣቸው ሕይወቶች (የክርስቲያን ትኩረት ጽሑፎች፣ 2010) አቅርበዋል።

---

**ዶ/ር ቆስጠንጢኖስ አር ካምቤል** በሥላሴ ወንጌላዊ መለኮት ትምህርት ቤት የአዲስ ኪዳን ተባባሪ ፕሮፌሰር ናቸው።

**ዶክተር ዲ.ኤ. ካርሰን** በሥላሴ ወንጌላዊ መለኮት ትምህርት ቤት የአዲስ ኪዳን ተመራማሪ እና የወንጌል ጥምረት መስራች ናቸው።

**ቄስ ሚካኤል ጄ. ግሎዶ** በኦርላንዶ፣ ፍሎሪዳ በሚገኘው የተሃድሶ ቲኦሎጂካል ሴሚናሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ተባባሪ ፕሮፌሰር ናቸው።

**ዶ/ር ሪቻርድ ሊንትስ** የቲዎሎጂ ፕሮፌሰር እና በጎርደን-ኮንዌል ቲኦሎጂካል ሴሚናሪ የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዝዳንት ናቸው።

**ዶ/ር ሾን ማክዶኖው** በጎርደን-ኮንዌል ቲኦሎጂካል ሴሚናሪ የአዲስ ኪዳን ፕሮፌሰር ናቸው።

**ዶ/ር ኤክሃርድ ጄ. ሽናቤል** በጎርደን ኮንዌል ቲኦሎጂካል ሴሚናሪ የሜሪ ኤፍ ሮክፌለር የአዲስ ኪዳን ጥናት ፕሮፌሰር ናቸው።

**ዶ/ር ማርክ ኤል ስትራውስ** በሳንዲያጎ ቤቴል ሴሚናሪ የአዲስ ኪዳን ፕሮፌሰር ናቸው።

# የቃላት ፍቺ

**ባሳር** - የዕብራይስጥ ቃል (ትርጉም) የምስራች ማምጣት ወይም ማወጅ ማለት ነው፣ በተለይም በጦርነት ውስጥ የድል ዜና

**ክርስቶስ** - "ክርስቶስ" ከሚለው የግሪክ ቃል "የተቀባ" ማለት ነው; ከብሉይ ኪዳን የዕብራይስጥ ቃል "መሲሕ" ጋር በቅርበት የተሳሰረ ነው

**ክሪስቶስ** - የግሪክ ቃል (ትርጉም) ለክርስቶስ; በሴፕቱጀንት ትርጉም "ማሺያክ" ወይም "መሲሕ" ማለት ሲሆን ትርጉሙም "የተቀባ" ማለት ነው።

**ፍጻሜ** - ክርስቶስ ተመልሶ የሚመጣበት እና ለታሪክ ሁሉ የእግዚአብሔርን የመጨረሻ ዓላማ የሚፈጽምበት የምስረታ ትምህርት ሦስተኛ እና የመጨረሻ ደረጃ

**ቀጣይነት** - የተመረቀ የኢሻቶሎጂ ሁለተኛ ወይም መካከለኛ ደረጃ; ከክርስቶስ የመጀመሪያ መምጣት በኋላ የእግዚአብሔር መንግሥት ጊዜ ግን ከመጨረሻው ድል በፊት

**ኢቫንግሊዮን** - የግሪክ ቃል (ትርጉም) ለ"ወንጌል"; በጥሬው "መልካም ዜና"

**ወንጌል**- በጥሬው "የምስራች"; የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ ምድር የመጣችው በኢየሱስ ማንነትና ሥራ እንደሆነ እና እግዚአብሔር ኢየሱስን እንደ መሲህ ለሚቀበሉትና ለሚታመኑት ድነትን ሲሰጥ ወደ ፍጻሜው እንደሚሰፋ ማስታወቂያ

**የተመረቀ የመጨረሻው ትምህርት** - የሚመጣው ዘመን መጀመሩን የሚናገረው ("ተመረቀ") የሚለው የፍጻሜ ዘመን እይታ፣ ነገር ግን ወደ ሙላቱ ገና አልመጣም። "ቀድሞውኑ፣ ገና ነው"

**ምረቃ** - በተመረቀ ኢሻቶሎጂ የመጀመሪያ ደረጃ; የክርስቶስን የመጀመሪያ መምጣት እና የሐዋርያቱን እና የነቢያትን አገልግሎት ያመለክታል

**የእግዚአብሔር መንግሥት** - በፍጥረት ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ሉዓላዊ እና የማይለወጥ አገዛዝ

ሜሺአክ - የዕብራይስጥ ቃል (ትርጉም) ለ"መሲህ"; የተቀባ

**መሲህ** - የዕብራይስጥ ቃል "የተቀባ" ማለት ነው; ከዚህ ዘመን ወደ መጪው ዘመን የሚሸጋገር ታላቁ ንጉሥ ከዳዊት ንጉሣዊ የዘር ሐረግ; በግሪክ "ክርስቶስ" ተብሎ ተተርጉሟል

**ኦላም ሃባ'** - የዕብራይስጥ ቃል (ትርጉም) "የሚመጣው ዘመን"; እግዚአብሔር ለእስራኤል የገባውን የተስፋ ቃል ሁሉ የሚፈጽምበትን የወደፊቱን ዘመን የሚያመለክት ረቢ ሐረግ

**ሆላም ሀዚህ** - የዕብራይስጥ ቃል (ትርጉም) ለ"ይህ ዘመን"; ከውድቀት ጀምሮ የነበረውን የአሁኑን የኃጢአት፣ የመከራ እና የሞት ዘመን የሚያመለክት ረቢ ሐረግ

**ሴፕቱጀንት** - የብሉይ ኪዳን የግሪክ ትርጉም

**ሉዓላዊነት** - የእግዚአብሔር ቀጣይነት ያለው አገዛዝ እና በፍጥረት ሁሉ ላይ ሙሉ ስልጣንን የሚያመለክት ሥነ-መለኮታዊ ቃል

**የሚመጣው ዘመን** - በእስራኤል ውስጥ ረቢዎች እና መሪዎች ከስደት በኋላ ስለሚመጣው የወደፊት የጽድቅ, የፍቅር, የደስታ እና የሰላም ዘመን ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ሀረግ; አምላክ ለታሪክ ያለው ዓላማ የሚፈጸምበት ጊዜ ነው።

**በዚህ ዘመን** - በእስራኤል ውስጥ ራቢዎች እና መሪዎች አሁን ያለውን የኃጢአት፣ የመከራ እና የሞት ዘመን ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ሐረግ

**ጽዮን** - የኢየሩሳሌም ሌላ ስም; አንዳንድ ጊዜ የዳዊት ከተማ ወይም የእግዚአብሔር ከተማ ይባላል; እንዲሁም ለመላው እስራኤል እና ለዘላለማዊቷ ወይም ለሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም መጠሪያ ጥቅም ላይ ይውላል



ቪዲዮዎችን፣ የትምህርት መመሪያዎችና ሌሎች ግብዓቶችን ለማግኘት Thirdmill at thirdmill.org. ይመልከቱ